# በኢሮብ ብሔረሰብ የህገረሰባዊ አስተዳደር መሪ (ኦና) መረጣ ሰርአተ-ክዋኔ ትንተና

በሥነ ጽሑፍና ፎክሎር ዘርፍ የሚሰጥ የማስተር አርት ዲግሪ ለማግኘት በከፊልማሟያ የቀረበ ጥናት

በ

ብርሃነ መድህን ንጉሰ

መቐለ ዩኒቨርሲቲ

የህብረተሰብ ሳይንስና ቋንቋዎች ኮሌጅ

የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ ጽሁፍ ትምህርት ክፍል (አማርኛ)

የፎክሎር ድህረ ምርቃ መርሃ ግብር

መጋቢት 2017 ዓ.ም.

መቐለ

**መቐለ ዩኒቨርሲቲ**

**የህብረተሰብ ሳይንስና ቋንቋዎች ኮሌጅ**

**የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ ጽሁፍ ትምህርት ክፍል (አማርኛ)**

# በኢሮብ ብሔረሰብ የሀገረሰባዊ አስተዳደር መሪ (ኦና) መረጣ ሰርአተ-ክዋኔ ትንተና

**በሥነ ጽሑፍና ፎክሎር ዘርፍ የሚሰጥ የማስተር አርት ዲግሪ ለማግኘት በከፊል ማሟያ የቀረበ ጥናት**

**በ**

**ብርሃነ መድህን ንጉሰ**

**አማካሪ**

**መሰለ ሙሉጌታ(ዶ/ር)**

**መጋቢት** 2017 **ዓ.ም.**

**መቐለ**

**መቐለ ዩኒቨርሲቲ**

**የህብረተሰብ ሳይንስና ቋንቋዎች ኮሌጅ**

**የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ ጽሁፍ ትምህርት ክፍል (አማርኛ)**

**በኢሮብ ብሔረሰብ የሀገረሰባዊ አስተዳደር መሪ (ኦና) መረጣ ሰርአተ-ክዋኔ ትንተና**

**በሥነ ጽሑፍና ፎክሎር ዘርፍ የሚሰጥ የማስተር አርት ዲግሪ ለማግኘት በከፊል ማሟያ የቀረበ ጥናት**

**በ**

**ብርሃነ መድህን ንጉሰ**

**መጋቢት 2017 ዓ.ም.**

**መቐለ**

**የፈተና ቦርድ አባላት**

| | | |
|---|---|---|
| 1.የውጭ ፈታኚ ስም | ፊርማ | ቀን |
| .................................. | ............................. | ..................... |
| 2.የውስጥ ፈታኚ ስም | | |
| ...................................... | .............................. | ...................... |
| 3. ዋና አማካሪ | | |
| ................................. | .............................. | ....................... |
| 4. ረዳት አማካሪ | | |
| ........................... | ............................... | ........................ |

## ምስጋና

ከሁሉ አስቀድሜ ለዚህ ያበቃኝን ፈጣሪ ከልቤ አመስግናለሁ ። በዚህ ጥናት ውስጥ በተለያየ መልኩ የበኩላቸውን ድጋፍ እና ትብብር ያደረጉልኝ ሰዎች ለሥራዬ መሳካት የነበራቸው ተሳትፎ የጎላ ነበር ። ከእነዚህም ውስጥ ከፍተኛውን ድርሻ የተወጣችሁ በሥነ-ፅሁፍና ፎክሎር የትምህርት ዘርፍ የተሻለ እውቀት እንዲኖረኝና በሁለቱ መካከል ያለውን ዝምድና በማስተማር የድርሻዬን እንድወጣ በቃላት በማይገለፅ በእውቀትም ሆነ በሞራል ድጋፍ ያገዛችሁኝ የኮርስ መምህራን እንዲሁም ጥናታዊ ፅሑፌን ያለመታከት በማረም ገንቢ አስተያየት ለሰጡኝ አስተማሬዬና አማካሪዬ ዶክተር መሰለ ሙሉጌታ ከልብ የመነጨ ምሥጋና አቀርባለሁ ።

**አጠቃሎ**

ይህ ጥናት በኢሮብ ብሔረሰብ የሀገረሰባዊ አስተዳደር መሪ (ኦና) መረጣ ስርአተ-ክዋኔ ትንተና ላይ ያተኮረ ሆኖ በዚህ ርዕሰ ጉዳይ ላይ ጥናት እንዳጠና ያነሳሱኝ ምክንያቶች በክዋኔው ላይ የሚታዩት ድርጊቶችና ተከታታይ ሁነቶች ፎክለራዊ ገፅታ እንዳላቸው መገንዘቤ እና በርዕሰ ጉዳዩ ላይ ጥናት እንዳልተካሄደ በመረዳቴ ነው።ጥናቱ አይነታዊ (Qualitative) ሲሆን የጥናቱ ዋና ዓላማ በኢሮብ ብሔረሰብ የሀገረሰባዊ አስተዳደር መሪ (ኦና) መረጣ ስርአተ-ክዋኔ ላይ አውድ ተኮር ትንታኔ ማድረግ ሲሆን አውድን መሰረት ባደረገ መልኩም ክዋኔው በቅደም ተከተል ተገልፀዋል።በተጨማሪም ከክዋኔው ጋር የሚመጡ ቃለ-ግጥሞች ተግባርና ቁሳዊ ባህሎች ትርጉም ታይቷል፤ የክዋኔውም ፋይዳ ተዳሷል።ጥናቱ የተሟላ እንዲሆን ቀዳማይና ካልኣይ የመረጃ ምንጮችን ተጠቅሟል።በምልከታ፣ በቃለ-መጠይቅ እና በቡድን ውይይት የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች መረጃዎቹ ተሰብስበዋል። የተገኙት መረጃዎችም በክዋኔ ንድፈ ሀሳብ በመታገዝ በገላጭ የትንተና ስልትተተንትነዋል። በትንተናውም ክዋኔው የቅድመ ዝግጅት እና በመረጣ ወቅትየሚከወኑ ስርአቶች ድምር ውጤት እንደሆነ ማንሳት ተችሏል።

የጥናቱ ግኝት የሚያመለክተው በኦና ሥነ ሥርዓት መሰረት የበላይ መሪ የሚሆነዉን ኦና ለመምረጥ የሚደረገዉ ቅድመ ዝግጅት፣በኦና መሾም ሂደት ላይ የሚፈጸሙክዋኔዎች፣የሚለበሱ አልባሳት፣የሚበሉ ባህላዊ ምግቦችና የሚጠጡ መጠጦች እንዲሁም የሚነገሩ ሰነ ቃሎች እየተከናወነ ያለውን ሂደት የሚጠቁሙ መሆናቸውታይቷል። በክዋኔ አማካይነት የሚተላለፉ መልዕክቶችም ለማህበረሰቡ የሚጠቅሙና ብሔረሰቡን የመግለጽ አቅማቸው ከፍተኛ መሆኑን ጥናቱ አመላክቷል።

በመጨረሻም የሀገረሰባዊ አስተዳደር መሪ (ኦና) መረጣ ስርአተ-ክዋኔ በመጥፋት ላይ ስለሚገኝየወረዳው ባህልና ቱሪዝም ለቀጣይትውልድሊተላለፍ የሚችልበት ይሁንታ ሀሳብ ቀርቧል።

## ማውጫ

ርዕስ ገፅ

ምስጋና.................................................................................. i

አጠቃሎ.................................................................................i i

### ምዕራፍ አንድ

መግቢያ..................................................................................1

1.1 የጥናቱ ዳራ...........................................................................1

1.2. የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት...............................................................2

1.3 የጥናቱ አላማ ..........................................................................3

1.3.1 የጥናቱ ዋና አላማ ......................................................................3

1.3.2 ዝርዝር አላማዎች......................................................................3

1.4 የጥናቱ የምርምር ጥያቄዎች..............................................................4

1.5 የጥናቱጠቀሜታዎች ......................................................................4

የጥናቱ ጠቀሜታ.........................................................................4

1.6 የጥናቱ ወሰን ..........................................................................5

1.7 የጥናቱ አወቃቀር........................................................................5

### ምዕራፍ ሁለት

2. የተዛማጅ ድርሳናት እና ቀደምት ጥናቶች ቅኝት.........................................6

2.1 የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት...............................................................6

2.2. ንድፈ ሀሳባዊ ዳራ....... .............................................................8

2.2.1. የክዋኔ ንድፈ ሀሳብ ........................................................8

2.2.1. 1.ክዋኔ............................................. ...........................10

2.1. 2.አውድ .........................................................................................12

2.1. 3.ከዋኝ ............................................................... 15

2.2.1. 4.ታዳሚ................. ......................................................................16

2.2.1. 5.ቴክስት ...... ...............................................................................17

2.3.ከበራ.........................................................................................17

2.3.1.የከበራባህሪያት ... ..................................................................20

2.4.ህገረሰባዊ አስተዳደር .................................................21

ምዕራፍ ሶስት

የአጠና ንዘዴ ...............................................................24

3.1 ምልከታ ................................................. .....................24

3.2 ቃለ መጠይቅ.............................................................................25

3.3 ተተኳሪ ቡድን ውይይት.......................................................................26

3.4 ሰነድፍተሻ..........................................................................................26

3.5 የናሙናአመራረጥዘዴ....................................................................26

3.6 የመረጃ አደረጃጀትና መተንተኛ ስልት.........................................................27

3.6.1 የመረጃ አደረጃጀት ስልት....................................................................27

## ምዕራፍ አራት

የኢሮብ ብሔረሰብ አጠቃላይ ዳራዎች እና በኢሮብ ብሔረሰብ የሀገረሰባዊ አስተዳደር መሪ (ኦና) መረጣ ሰርአተ-ክዋኔ ትንተና ...........................................................28

4.1.የኢሮብ ብሔረሰብ አጠቃላይ ዳራዎች...........................................................28

4.1.1 የኢሮብ ብሔረሰብ አመጣጥ ታሪክ...........................................................28

4.1.2 የብሔረሰቡ መልክዓ ምድራዊ አቀማመጥና አየር ንብረት.............................30

4.1.3 የብሔረሰቡ እምነትና አምልኮ...........................................................30

4.1.4 የብሔረሰቡ ቋንቋ...........................................................31

4.1.5 የብሔረሰቡ ኢኮኖሚያዊ ሁኔታ...........................................................31

4.2 ኦና ሰርአት...........................................................32

4.2.1 የኦና ሰርአት ህጎች ውጫዊ ገጽታ...........................................................33

4.2.2 የኦና ሰርአት ህጎች ውስጣዊ ገጽታ...........................................................34

4.3 የኦና ሰርአት መሰረታዊ ባህርያት...........................................................34

4.3.1 የኦና (መሪ) አመራረጥ ሰርአት ሂደት...........................................................36

4.3.1 .1 የሀገረሰባዊ አስተዳደር መሪ (የኦና) መረጣ ክዋኔ ቅድመ ዝግጅት..............37

4.3.1 .2 የሀገረሰባዊ አስተዳደር መሪ (የኦና) መረጣ መከወኛ ጊዜን መለየት...........37

4.3.2 ምስረታ ካቢኔ...........................................................45

4.3.3 የኦና ስልጣን ዘመን...........................................................46

## ምዕራፍ አምስት

5.1 ማጠቃለያ...........................................................48

5.2 የይሁንታ ሀሳብ...........................................................48

**ዋቢ ጽሑፎች**...............................................................................................49

**የመረጃ አቀባዮች ስም ዝርዝር**.......................................................................52

**አባሪ ፎቶዎች**.............................................................................................54

# ምዕራፍ አንድ

# መግቢያ

## 1.1 የጥናቱ ዳራ

ሀገረሰባዊ አስተዳደርን በተመለከተ ሙሁራን በርካታ ብያኔ ይሰጣሉ ። ከሙሁራን መካከል Nsarkoh ተጠቃሽ ነው ። Nsarkoh ሀገረሰባዊ አስተዳደር ከማዕከላዊ መንግስት አስቀድሞ የነበረ፣በልማዳዊ ህግና በአካባቢዊ ደንብ የሚመራ ሰርአት ነው በማለት ጽፏል። (Nsarkoh 1964:13) (Cowan 1995:4-5) የተባለው ፀሀፊ ደግሞ የአፍርካ ህዝቦች ሀገር በቀል የአስተዳደር ስርአቶች የሚጋሯቸው ባህሪያት እንዳሏቸው ያስረዳል ።ከነዚህ መለያ ባህሪያት መካከል አንዱ በሀገረሰባዊ ንጉሥ ወይ በባለአባት የሚመሩ መሆናቸውንይጠቅሳል።

Cowan በተጨማሪ ብዙ የአፍርካ ህዝቦች የማህበረሰቡ ልማድ እና ደንብ የማያከብሩ ሀገረሰባዊ መሪዎቻቸውን የሚቆጣጠሩበት ሀገረሰባዊ ሰርአት እንደነበራቸው እና የሚያስተዳድራቸው ሰርአቱን በበላይነት የሚመራው እድሜን መሰረት አድርገው ይወክሉ እንደነበረ ያስረዳል (Cowan,1959:5)።

ሰርአተ ከበራዎች በምንም ምክንያት ይከበሩ ክዋኔ አላቸው። ከዚህ ጋር በተያያዘም የክዋኔና የከበራ ትስስርን በተመለከተ ከበራ ከሌለ ክዋኔ እንደማይኖርና ክዋኔ በራሱ ግልጽ የሆነ መልዕክት ያለው ድርጊት መገለጫው እንደሆነ (Rappaport, 1992, 25) "ምንም ክዋኔከሌለ፣ ምንም አይነት የሥርዓት ከበራአይኖርም፣ ክዋኔ በራሱ የሚፈጸመውበሥርዓተ ከበራ ውስጥ ስለተመዘገቡት ነገሮች መልእክት በትክክል ለማስተላለፍ ነው።"በማለት ያስቀምጣሉ።

የክዋኔን ንድፈ ሀሳብ አስመልክተው የሚሰጡ ማብራሪያዎች ከተለያዩ አቅጣጫዎች የተቃኙ ናቸው። የአንዳንዶቹ የክዋኔ ንድፈ ሀሳብ ክዋኔው የተከሰተበትን አጋጣሚና የአከዋወኑን ጥበባዊነት ደረጃ ይመለከታል። በዚህ አይነቱ አመለካከት የውበት ጉዳይ ግድ የሚለው ነው። ከክዋኔው ውስጥም ክዋኔው የቀረበበትን ቋንቋ ግልጽነት፣ የንግግሩን ሂደትና የከዋኞቹን ስልት በትኩረት ይመለከታል። በዚህ ዓይነቱ አተያይጥናቱ መደረግ ያለበት ከባህሉ፣ ከቋንቋው በወጡ ሰዎች ነው። ስለሆነም ውስጥ አዋቂ አጥኚ ያስፈልገዋል። በዚህ ንድፈ ሀሳብ መሰረት ከክዋኔው አስቀድመው የተሰበሰቡ ጥሬ ነገሮች በሙሉ ጥበብ አልባ እንደሆኑ ተደርገው

ይወሰዳሉ። ማንኛውም ክዋኔ በከዋኙ ብቃት ላይ የሚመሰረት ነው። በሚከሰተው እያንዳንዱ ክስተት ላይ ከዋኙ ሁኔታዎችን እየተመለከተ የመለዋወጥ ሃላፊነት አለበት። እነዚህ ሁኔታዎችም መቼቱንና ታዳሚውን እየተመለከተ እንዲቀበሉ ትወናውን የማመቻቸት ኃላፊነቱን የሚያመላክቱ ናቸው። ፎክሎር ትዕምርታዊ እንደመሆኑ፣ ከባህል ጋር እንደመታሰሩ ከተግባር ጋር የተያያዘና የሰውን ባህሪ እንደማሳየቱ መጠን እነዚህን ነጥቦች በትኩረት ማየት እንደሚያስፈልግ (Bauman, 1982, 2) ይገልጻል።

ሌላው የክዋኔ ንድፈ ሀሳብ አቅጣጫ ስነ-ሰብዓዊ (Anthropologic) የክዋኔ አጠናን አቅጣጫ ነው። ይህ ደግሞ ክዋኔን የሰውን ሁለንተናዊ ባህሪ የመግለጫ መንገድ አድርጎ ይወስደዋል። በዚህ አጠናን አቅጣጫ ተጠቃሽ የሆኑት ምሁር (Schechner, 1988) ናቸው። አንድ ከዋኝ ከሌሎች ከዋኞች ጋር አብሮ የመስራት ችሎታና ፈቃደኝነት ሊኖረው ይገባል። እንዲሁም ከተመልካቹ፣ ከአድማጩ፣ በአጠቃላይ ከታዳሚው ጋር እነሱን በማሳተፍ መልኩ ቢከወን ተመራጭ ነው። ከዋኙ ሌሎች ደጋፊዎችን በመያዝ ወይም ለብቻው ታዳሚ ባለበት ወይም በሌለበት ሊከወንም ይችላል። የክዋኔ ንድፈሀሳብ የአጠናን ሂደት የበለጠ ውጤታማ የሚሆነው ዘዴ በተግባር በአካል በመስኩ ላይ በመገኘት ከተጠኚው ማህበረሰብ እውነተኛ የህይወት ተሞክሮ በመቅዳትና በመተንተን ነው።

ሀገረሰባዊ የአስተዳደር መሪ (ኦና) መረጣ ስርአተ የአከባቢዉ ከፍተኛ መሪን የመምረጥ እና በሰርአቱ የመመራት ሂደት ሆኖ የኢሮብ ህዝብ በጋራ በፈጠረው ሕግና ደንብ የተደራጀ ብሔረሰብ ነበር::የኢሮብ ብሔረሰብ ባህላዊ የአስተዳደር ሰርአት የሆነው የኦና ሥርዓት ከኢሮብ ብሔር ሁለንተናዊ ሕይወትና ዕድገት ጋር በእጅጉ ተያያዘ፣ ከቀላል እስከ ውስብስብ ወደሆነ ማህበራዊ ጉዳዮች የሚዳስስ ባህላዊ አስተዳደር ነው። ኦና ሰርአት ብሔረሰቡ ራሱን በራሱ የሚያስተዳደርበት የጋራ ሰርአቱ ነው። (ዝግታ ሓድጉ 2008፣2)

## 1.2 የጥናቱ አነሳሽ ምክንያቶች

ይህ ጥናት በኢሮብ ብሔረሰብ የሀገረሰባዊ አስተዳደር መሪ (ኦና) መረጣ ስርአተ-ክዋኔ ትንተና ላይ ያተኮረ ሆኖ በዚህ ርዕሰ ጉዳይ ላይ ጥናት እንዳጠና ያነሳሱኝ ምክንያቶች የፎክሎር ኮርሶችን በሚማርበት ወቅት በኢሮብ ብሔረሰብ የኦና ሰርአት አተገባበር ማሻሻያ ለማድረግ በብሔሰቡ ታላላቅ ሽማግሌዎች በ 2016 ዓ.ም በተካሄደው ምክክር መድረክበተሳተፍኩባቸው ጊዜያት በተመለከትኳቸው ክንውኖች ላይ የሚታዩት ድርጊቶችና

ተከታታይ ሁነቶች ፎክሎራዊ ገፅታ እንዳላቸው መገንዘቤ እና በርዕሰ ጉዳዩ ላይ ጥናት እንዳልተካሄደ በመረዳቴ ነው።

## 1.3. የጥናቱ ዓላማዎች

### 1.3.1 የጥናቱ ዋና ዓላማ

በኢ.ሮብ ብሔረሰብ የሀገረሰባዊ አስተዳደር መሪ (ኦና) መረጣ ስርአት-ክዋኔ ላይ ትንተና ማድረግ ነው።

### 1.3.2 ዝርዝር ዓላማዎች

- የኢ.ሮብ ብሔረሰብ የሀገረሰባዊ አስተዳደር መሪ (ኦና) መረጣ ስርአት-ክዋኔ ምን እንደሚመስል በሁነቶቹ ላይ በመመስረት የክዋኔውን አውድበቅደምተከተል ማጥናት፣
- በኢ.ሮብ ብሔረሰብ የሀገረሰባዊ አስተዳደር መሪ (ኦና) መረጣ ስርአት-ክዋኔ ወቅት አገልግሎት ላይ የሚውሉ ቁሳዊ ባህሎችን ትርጉም መግለጽ (ለምን ትዕምርት እንደዋለመግለጽ)፣
- ክዋኔው ላይ የሚዜሙ ወይም የሚነገሩ ቃል ግጥሞች እንዴትና ለምንእንደሚቀርቡ ተግባራቸውን በማጤን ማሳየት፣
- የክዋኔው ተሳታፊዎች ለከበራው (የሀገረሰባዊ አስተዳደር መሪ (ኦና) መረጣ ስርአት) ያላቸውን አመለካከትመግለጽ፣
- የስርአቱ ታዳሚዎች በክዋኔው ላይ በመሳተፋቸው የሚያገኙትን ጥቅም መግለጽና፣
- የሀገረሰባዊ አስተዳደር መሪ(ኦና)መረጣ ስርአት ክዋኔን ፎክሎራዊ ተግባር ማብራራት እና መሰነድ ናቸው።

### 1.4. የጥናቱ የምርምር ጥያቄዎች

1. ሀገረሰባዊ የኦና ሰርአት ምንድን ነው?

2.የሀገረሰባዊ አስተዳደር መሪ (ኦና)መረጣ ስርአተ ክዋኔአወቃቀር ምን ይመስላ? ወይም ክዋኔው የምን የምን ሁነቶች ድምር ውጤት ነው?

3. ለሁነቶቹ መፈጠርና መከወን ምክንያቶቹ ምን ምን ናቸው?

4.በሀገረሰባዊ አስተዳደር መሪ(ኦና) መረጣ ስርአተ ክዋኔ ላይ ተሳታፉዎች እንዴት ይሳተፋሉ?

5. በሀገረሰባዊ አስተዳደር መሪ(ኦና) መረጣ ስርአተ ክዋኔፋይዳምንድን ነው?

6. በሀገረሰባዊ አስተዳደር መሪ (ኦና) መረጣ ሰርአት ማህበረሰቡ የሚሰጠው ትርጉም ምንድን ነው?

### 1.5. የጥናቱ ጠቀሜታዎች

ይህ ጥናት በርካታ ጠቀሜታዎች ይኖሩታል ። ከጠቀሜታዎቹ መካከል በዋናነት የሚከተሉት ናቸው።

- ኦና ሰርአት አካባቢያዊ፣ታሪካዊ ጉዳዮችና እንዲሁም በሀገረሰባዊ አስተዳደር ውስጥ የሚገኙ ተፈጥሯዊ፣ቃላዊ፣ቁሳዊናመንፈሳዊ ሀብቶችን ማስተቃቀቅ።
- የሀገረሰባዊ አስተዳደር ክዋኔ በመጥፋት ላይ ስለሚገኝ ክዋኔውን ከነቃል-ግጥሞቹ በቅደም ተከተል በማሳየት በሰነድነት ያስቀምጣል።
- የከበራው ክዋኔ መጠናት ለፎክሎር ጥናት መስክ አውንታዊ አስተዋጽኦ ያበረክታል።
- በዚህ ርዕሰ ጉዳይ ዙሪያ ሰፊ ጥናት ማድረግ ለሚሹ ሰዎች እንደ መነሻ በመሆን ያገለግላል።
- የሀገረሰባዊ አስተዳደር ክዋኔን ባህላዊና ማህበራዊ አውድማወቅ ለሚፈልጉ መረጃ ይሰጣል።

## 1.6. የጥናቱ ወሰን

ኢሮብ ብሔረሰብ በኢትዮጵያ እና በኤርትራ የሚገኝ ብሔረሰብ ነው።ይህ ጥናት ትኩረት ያደርገው በኢትዮጵያ በትግራይ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት በምስራቅ ትግራይ በሚገኘዉ ብሔረሰብ ላይ ብቻ ነው።ይህ ቦታእናብሔረሰብ የመረጥኩበት ምክንያት በኢሮብ ብሔረሰብ የሀገረሰባዊ አስተዳደር መሪ (ኦና) መረጣ ስርአተ ለዘመናት ስተዳደሩ የኖሩ ብዛትያላቸው የብሔረሰቡ ኣባላት የሚገኙበት በመሆኑነው። ከርእሰ ጉዳይ አንጻር ደግሞ ይህ ጥናት በብሔረሰቡ የሀገረሰባዊ አስተዳደር መሪ (ኦና) መረጣ ስርአተ-ክዋኔ ላይ ትንተና ላይ ብቻ ትንተና አድርጓል።

## 1.7. የጥናቱ አወቃቀር

ይህ ጥናታዊ ጽሁፍ አምስት ምዕራፎች አሉት ። የመጀመሪያው ምዕራፍ የጥናቱን አጠቃላይ ንድፍ ይይዛል ። በውስጡም የጥናቱ ዳራ፣አነሳሽ ምክንያት፣የጥናቱ ዓላማዎች፣የምርምር ጥያቄዎች፣የጥናቱ ፋይዳዎች፣የጥናቱ ወሰን፣የአጠናን እና መረጃ አሰባሰብ ዘዴን የያዘ ነው።

ምዕራፍ ሁለት የክልሳ ድርሳናት የሚቀርቡበት ነው ። ጥናቱን ለማከናወን የሚረዱ ንድፈ ሀሳባዊ ዳራ የሚቀርቡበት ነው፤እንዲሁም ከጥናቱ ጋር በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪግንኙነትያላቸው ቀደምት ጥናቶች የሚዳሰሱበት ነው። ምዕራፍሶስት የአጠናን ዘዴ፤ምዕራፍ አራት ለጥናት የተመረጠውን የኢሮብ ብሔረሰብ አጠቃላይ ዳራ የሚያስተዋውቅና የተሰበሰቡት የኦና ሰርአት ክዋኔዎችን ትንተና ይይዛል።በውስጡም ስለብሔረሰቡ አመጣጥ ታሪክ፣ቋንቋና እምነት፣መልከዓ ምድር፣የአየር ንብረትና ስነህዝብ፣ኢኮኖሚ እና እሴት የሚመለከቱ መረጃዎችን እና የክዋኔ ትንታኔን አካትቷል።

ምዕራፍ አምስት የጥናቱ ማጠቃልያና የይሁንታ ሀሳቦች የሚቀርቡበት ይሆናል። በመጨረሻም ዋቢ መፃህፍትና የተጠቀሱ ጥናታዊ ፅሑፎች እንዲሁም አባሪ ፎቶግራፍች ቀርቦበታል።

# ምዕራፍ ሁለት

# የተዛማጅ ድርሳናት እና ቀደምት ጥናቶች ቅኝት

ይህ ምዕራፍ ከጥናቱ ጋር ተዛማጅነት ያላቸው ስራዎች የተቃኙበትና የንድፈ ሀሳባዊ ዳራ የቀረበበት ነው።

## 2.1. የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት

በጥናቱአነሳሽ ምክንያት ላይ እንደተገለጸው በኢሮብ ብሄረሰብ ላይ የተደረጉ ፎክሎራዊ ጥናቶች በቁጥር እጅግ አነስተኛ ናቸው። በተለይም ትኩረታቸው በኢሮብ ብሔረሰብ ሰርአተ ክዋኔ ላይ ያደረጉ ጥናቶችማግኘት አልቻልኩም ። ነገር ግን አንድ ከእኔ ጥናት ጋር ተመሳሳይ የሆነ ለትግራይ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ኣካዳሚ ቋንቋዎች በ2009 ዓ/ም በአቶ ተስፋይ ካሕሳይ የቀረበ የይዘት ግንኙነት ያለዉ አንድ ጥናታዊ ጽሁፍ ላቅርብ::

ጥናቱ የኢሮብ ብሔረሰብ **ኦኒ ሰርዓት**በሚል ርእስ በ2009 ዓ.ም በሳሆ ቋንቋ በተስፋይ ካሕሳይ የተጠና ጥናት ስሆን የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ የኢሮብ ብሔረሰብ **ኦኒ ሰርዓት**ያለዉ ትርጉም መግለጽና መተንተን ነው።

ጥናቱ አይነታዊ (Qualitative) ሲሆን የጥናቱን አላማ ለማሳካት ተመራማሪዉ የምርምር ሂደቶችን ማለትም የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት፣ የጥናቱ አላማ፣ የጥናቱ ወሰን፣ የጥናቱ ፋይዳ፣ ክልሰ ድርሳናት፣ የአጠናን ዘዴ እና የመረጃ መተንተኛ ስልት በግልጽና ያልተካተተበትና በመሆኑ ከእኔ ጥናት በምርምር ሂደትና መረጃ መተንተኛ ማእቀፍ የሚለይ ስሆን ይህ ጥናት ከእኔዉ ጥናት ጋር የሚመሳሰለዉ በአጠቃላይ የኦና ሰርአተ ላይ ያተኮረ ጥናት መሆኑ ነዉ።

ለቺሳ (በ1982 ዓ.ም.) በጨሊያ አውራጃ ስለ ውቃቢ ያለው እምነትና የእምነቱ መገለጫ ግጥሞች "በሚል ርዕስ በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነ-ጽሁፍ ት/ክፍል ለአርትስ ባችለር ዲግሪ ማሟያነት ጥናት አቅርቧል። ጥናቱ ስለውቃቢ ምንነት ማብራሪያ ይሰጣል። እንዲህም የጨሊያ አውራጃ ነዋሪዎች ስለውቃቢ ያላቸውን አመለካከትና እምነት ስርዓት የሚገልፅ ሲሆን የእምነቱ መገለጫ በሆኑት የቃል ግጥሞች ላይ ትንተና አድርጓል። ጥናቱ ግጥሞቹን በመገኛ ቋንቋቸው ማለትም በኦሮምኛ ቋንቋ ሰብስቦ ወደ አማርኛ በመተርጎም ከቅርፅና ከይዘት አንፃር ቃኝቷል። ጥናቱ ያነሳው ጉዳይ አንድ የመንፈስ አይነት የሆነውን ውቃቤን ቢሆንም የመንፈሱ መገለጫ የሆኑት ቃል ግጥሞች መገኛ ስለሆነው ክዋኔ አያነሳም።

በወልዱ (1991 ዓ.ም.) "የዛር ትያትራዊ ክንውን ሲሚዩቲክስ ትንተና" በሚል ርዕስ ያቀረበው ጥናት የውቃቢ፣ የአዶ ከበሬና የዛር ስርዓት ክንውን አንድነትና ልዩነት በመጠኑ የተገለፀበት ነው። የቀጨኔው "ሻንቆ" ዛር ስርዓተ ክንውን አጠቃላይ ዕይታ በሚል የስርአቱ የፍርድ ክዋኔ ላይ ትንታኔ ሰጥቷል።በሶስተኛው ምዕራፍ የቀረበው የዛር "ሲዩሚዩቲክ ትንተና" ሲሆን ከዚህ ጥናት ጋር ተዛምዶ የለውም። በጥናቱ ላይ ዛርና ውቃቢ የተለያዩ መሆናቸውን ለማሳየት ሞክሯል።

በየውልሰው (1992 ዓ.ም.) "አዋቂና የጥንቆላ ስራው በደብረ-ማርቆስ አካባቢ" በሚል ርዕስ ያቀረበው ጥናት ስለአዋቂ ምንነት፣ ስለ ዛር ምልመላና ስለጥንቆላ ስራ የክዋኔ ሂደት የዛር መቀበያ፣ የፍርድ ቀን እና የዛር መሸኛ የተሰኙ ሶስት የክዋኔ ደረጃዎች እንዳሉት ገልጿል። በመጨረሻም ቃላዊ ግጥሞች የክዋኔውን ሂደት ተከትለው እንደሚዜሙና ዛር ቶሎ እንዲወርድ የሚለምኑ ብሎም የአስጠንቋዮችን ችግር የሚያንፀባርቁ መሆናቸውን በመግለፅ ጥናቱ ተጠናቅቋል። ይህ ጥናት ከእኔ ጥናት ጋር የሚመሳሰለው ስለ ዛር የክዋኔ ደረጃዎች በሚያትተው ክፍሉ የዛር መቀበያና መሸኛ በሚል ባነሳቸው አንዳንድ ሀሳቦች ብቻ ነው። ስለጥንቆላ እና ስለዛር ፍርድ የሚያትተው የጥናቱ ዋና ዓላማም ሆነ በርዕሰ ጉዳዩ የተለያየ ነው።

በእንዳልካቸው (1993 ዓ.ም.) "በምዕራብ ሀረጌ (ጨርጨር) አካባቢ የአወሊያ ቤት የልመና ግጥሞች የይዘት ትንተና በሚል የቀረበው ጥናት ደግሞ ዋና ትኩረቱ የአውሊያ ቤት የልመና ግጥሞችን ይዘት መተንተን ነው። ይህ ጥናት ከእኔ ጥናት ጋርየሚመሳሰለው የልመና ክዋኔውን በተወሰነ መልኩ ለማሳየት በመሞከሩና የመገልገያ ቁሶችን ትዕምርት ስለሚገልፅ ነው። ጥናቱ የአውሊያ ቤት የልመና ግጥሞች ይዘት በተለያዩ ንዑሳን ርዕሶች ተከፋፍሎ ተተንትኗል። የአውሊያ ቤት የልመና ግጥሞች የአውሊያን ጥንካሬ፣ ትሁትነት፣ ፈጥኖ ደራሽነትና ሁሉን አዋቂነት የሚገልፁ መሆናቸው በማጠቃለያ ሀሳብነት በማቅረብ ተጠናቅቋል። አውሊያና ዛርን እንደ አንድ የመንፈስ መጠሪያ አድርጎ በተተኪነት መጠቀምን እንደክፍተት አይቸዋለሁ።

በተመስገን (1995 ዓ.ም.) "የዛር ትውፊት እና በውስጡ የሚገኙ ቴአትራዊ አላባውያን በራያና ቆቦ አካባቢ" በሚል ርዕስ በትያትር ጥበባት ትምህርት ክፍል የቀረበው ጥናት "የዛር ትውፊታዊ ክንውን ትያትራዊ (ድራማዊ ይዘት)" የተተነተነበት ነው። ይህ ጥናት ከእኔ ጥናት ጋር ክዋኔን ባሳየበት ክፍል የሚመሳሰል ቢሆንም ዋና ዓላማው "ትያትርን እና የዛር ትውፊታዊ ክዋኔን በማዛመድ በዛር ትውፊታዊ ክዋኔ ውስጥ የሚገኙ ተውኔታዊ አላባዎችን ነቅሶ ማውጣት

እና የሁለቱን የዝምድና ባህሪያት መተንተን/መመልከት" በመሆኑ ይለያያል። ትንተናውም ትኩረቱን ያደረገው የዛር ክዋኔን ከትያትር ጋር በማነፃፀር ተውኔታዊ አላባዎቹን ለይቶ ማሳየት ላይ እንጂ ፎክሎራዊ ገፅታን ማሳየት አይደለም።

## 2.2. ንድፈ ሀሳባዊ ዳራ

ይህ ክፍል ለዚህ ጥናት ርዕሰ ጉዳይ ንድፈ ሀሳባዊ ማዕቀፍ በመሆን የሚያገለግለውን የክዋኔ ንድፈ ሀሳብን /performance theory/ እና ከዚህ ንድፈ ሀሳብ ጋር ተያይዘው የሚነሱ ፅንሰ ሀሳቦች (concepts) ላይ ማብራሪያ የተሰጠበት ነው።

የክዋኔ ንድፈ ሀሳብ በማዕቀፍነት የተመረጠበት ምክንያት የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ የገፈራ ስርዓቱን አጠቃላይ ክዋኔ ማሳየት በመሆኑ ነው። ይህን ዓላማ ከግብ ለማድረስ የሚረዳ ንድፈ ሀሳባዊ ማዕቀፍ ደግሞ የክዋኔ ንድፈ ሀሳብ ነው።

### 2.2.1. የክዋኔ ንድፈ ሀሳብ

የክዋኔን ንድፈ ሀሳብ አስመልክተው የሚሰጡ ማብራሪያዎች ከተለያዩ አቅጣጫዎች የተቃኙ ናቸው። የአንዳንዶቹ የክዋኔ ንድፈ ሀሳብ ክዋኔው የተከሰተበትን አጋጣሚና የአከዋወኑን ጥበባዊነት ደረጃ ይመለከታል። በዚህ አይነቱ አመለካከት የውበት ጉዳይ ግድ የሚለው ነው። ከክዋኔው ውስጥም ክዋኔው የቀረበበትን ቋንቋ ግልጽነት፣ የንግግሩን ሂደትና የከዋኞቹን ስልት በትኩረት ይመለከታል። በዚህ ዓይነቱ አተያይጥናቱ መደረግ ያለበት ከባህሉ፣ ከቋንቋው በወጡ ሰዎች ነው። ስለሆነም ውስጥ አዋቂ አጥኚ ያስፈልገዋል። በዚህ ንድፈ ሀሳብ መሰረት ከክዋኔው አስቀድመው የተሰበሰቡ ጥሬ ነገሮች በሙሉ ጥበብ አልባ እንደሆኑ ተደርገው ይወሰዳሉ። ማንኛውም ክዋኔ በከዋኙ ብቃት ላይ የሚመሰረት ነው። በሚከሰተው እያንዳንዱ ክስተት ላይ ከዋኙ ሁኔታዎችን እየተመለከተ የመለዋወጥ ሃላፊነት አለበት። እነዚህ ሁኔታዎችም መቼቱንና ታዳሚውን እየተመለከተ እንዲቀበሉ ትወናውን የማመቻቸት ኃላፊነቱን የሚያመላክቱ ናቸው። ፎክሎር ትዕምርታዊ እንደመሆኑ፣ ከባህል ጋር እንደመታሰሩ ከተግባር ጋር የተያያዘና የሰውን ባህሪ እንደማሳየቱ መጠን እነዚህን ነጥቦች በትኩረት ማየት እንደሚያስፈልግ (Bauman, 1982, 2) ይገልጻል።

የክዋኔ ንድፈ ሀሳብ የአሜሪካዊያን የፎክሎር እና የነገረ-ሰብ ባለሙያዎች ያደረጉት እንቅስቃሴ ሲሆን የምዕራባዊያንን ሜታፊዚካል አስተሳሰብ በመቃወም የተነሳ ነው። በዋነኛነት ትርጉምን አንድ ማዕከል በመፍጠር ከእርሱ አንፃር መፈከር እንዲሁም ምንጬን በግለሰብ

ደረጃ መወሰንን፣ ተጨባጭ በሚባል ቴክስትና አውድ ላይ መመስረትን በመቃወም በቋንቋና በማህበረሰባዊ ህይወት ላይ በማተኮር ማዕከልን ማፍረስ እና በሌላ አተያይ ትርጉምን መፈከር ላይ ትኩረት አድርጎ መነሳቱን (Bauman እና ሌሎችም፣ 1990፣ 61) ገልጸዋል።

ይህን ንድፈ ሀሳብ ለፎክሎር ባለሙያዎች በማስተዋወቅ ደረጃ መስራት ችሏል በመባል በቀዳሚነት የሚጠቀሱት Richard Bauman ናቸው (Sims እና Stephen ፣ 2005፣ 128)። አቀራረቡ መሰረት ያደረጋቸው በርካታ እሳቤዎች ሲኖሩ ከእነዚህ መካከልም ፎክሎር ተግባራዊ የሚሆነው በተከሰተበት ጊዜ ባለው ክዋኔ ወይም ተግባቦት እንጂ በቴክስቱ ብቻ መሆን የለበትም፣ ሁሉም ተግባር/ሁነት መመዝገብ ይኖርበታል፤ ምዝገባው አድካሚ ቢሆንም ገላጭ የሆኑ መረጃዎችንም መጨመር ያስፈልጋል የሚሉት ይጠቀሳሉ።

The folklore concepts apply not to a text but to an event in time in which a tradition is performed or communicated. Hence the whole performance or communicative act must be recorded. However, recording "events" often amounted to little more than taking extradirt from around the root wad. (Hufford, 1995, 528)

አቀራረቡ ቃላዊ ጥበብ ላይ ትርጉም ሲሰጥ ቢታይም በክዋኔ ወቅት አገልግሎት ላይ የሚውሉ ቁሶችና ከእነሱ ጋር ያለው ግንኙነት እንዲሁም ባህሪን፣ አመለካከትን እና ድርጊትን ጨምሮ ለመቃኘት ያስችላል። በተጨማሪም መንፈሳዊ፣ ቁሳዊ እና ቃላዊ ባህሪያቱንም ጥናቱ ይመለከታቸዋል። አጥኚውም የተፈፀመውን ተግባርና ተግባቦት መነሻ አድርጎ በሰላና በነቃ መንፈስ ምልከታውን የተለያዩ መረጃ መሳሪያዎችን በመጠቀም መከታተል ይጀምራል። ለሁሉም እኩል ዕድል በመስጠት በዋነኛነት ግቡ የሆነውን ከዘወትራዊ ህይወት ውጭ የሚመጣውን ተፅዕኖ ለማግኘት በሚያስችለው መልኩ ጥያቄውን ይጠይቃል። በዙሪያው ያሉ ቁሳሶዎች፣ ጌጣጌጦች፣ ስዕሎች እና ምልክቶች ምን ግንኙነት አላቸው? በትርጉም ላይስ የሚያመጡት ለውጥ አለ? ብሎ ለማየት ያስችለዋል። ወደ አውዱ በማተኮርም ምዕራባዊያን እንደ ተጨባጭና ያልተበረዙ አድርገው የሚወስዱትንና ቴክስት የት ይጀምራል? አውዱስ መቼ ይገባል? ብለው ለሚያነሱት ጥያቄ ለሁለቱም እኩል ዕድል በመስጠት ራሳቸውን የሚገልፁበትን ሌላ ስያሜ በመስጠት ያጠኑበታል። ለቴክስት (entextualization) ፣ ለአውዱ ደግሞ /contextualization/ የሚል አቻ መጠሪያ በመስጠት ምዕራባውያን ለውጤት

ትኩረት ሰጥተው የሰሩበትን መንገድ በመቃወም እና በመተው ሂደቱ ላይ ትኩረት እንዲሰጥበት አድርገዋል። (Richard Bauman, 1990, 68)

ባህሉን ለመተርጎምም ከዋኝ ተኮር የሆነውን አቀራረብ ብቻ ሳይሆን ተደራሲንም በማካተት ሁለቱንም እንደ አንድ ትርጉም አስገኝ በመጠቀም በሂደቱ ላይ የነበረውን የሁለቱን ግንኙነት መሰረት በማድረግ ጥያቄዎችን ያነሳል። ሂደቱ ተግባቦታዊ በመሆኑ አዋኚው ትርጉሙን የሚያመጣው ውጫዊም ሆነ ማህበራዊ አውዱ በሚመርጠው ሳይሆን በስምምነቱ ላይ በመመስረት ነው (ዝኒ ከማሁ፣ 1990፣ 62-70) ይላሉ።

ሌላው የክዋኔ ንድፈ ሀሳብ አቅጣጫ ስነ-ሰብዓዊ (Anthropologic) የክዋኔ አጠናን አቅጣጫ ነው። ይህ ደግሞ ክዋኔን የሰውን ሁለንተናዊ ባህሪ የመግለጫ መንገድ አድርጎ ይወስደዋል። በዚህ አጠናን አቅጣጫ ተጠቃሽ የሆኑት ምሁር (Schechner, 1988) ናቸው። አንድ ከዋኝ ከሌሎች ከዋኞች ጋር አብሮ የመስራት ችሎታና ፈቃደኝነት ሊኖረው ይገባል። እንዲሁም ከተመልካቹ፣ ከአድማጩ በአጠቃላይ ከታዳሚው ጋር እነሱን በማሳተፍ መልኩ ቢከወን ተመራጭ ነው። ከዋኙ ሌሎች ደጋፊዎችን በመያዝ ወይም ለብቻው ታዳሚ ባለበት ወይም በሌለበት ሊከወንም ይችላል። የክዋኔ ንድፈሀሳብ የአጠናን ሂደት የበለጠ ውጤታማ የሚሆነው ዘዴ በተግባር በአካል በመስኩ ላይ በመገኘት ከተጠኚው ማህበረሰብ እውነተኛ የህይወት ተሞክሮ በመቅዳትና በመተንተን ነው።

በንድፈ ሀሳቡ ላይ የሚነሱት ሀሳቦች የተለያዩ እንደመሆናቸው ከክዋኔ ንድፈ ሀሳብ ጋር ተያይዘው የሚነሱት የክዋኔ፣ የአውድና የቴክስት ፅንሰ ሀሳቦችም የተለያዩ ናቸው። በመሆኑም ለእነዚህ ፅንሰ ሀሳቦች ማብራሪያ መስጠት ያስፈልጋል።

### 2.2.1. 1.ክዋኔ

ክዋኔን የተለያዩ ምሁራን በተለያየ መንገድ በይነውታል። (Bauman, 1992, 14) በራሱ "performance usually suggests an aesthetically marked and heighted mode of communication, formed in a special way and put on display for an audience" በማለት ክዋኔ ለየት ባለ መንገድ የሚቀርብ ጥበባዊ የተግባቦት ስልት መሆኑን ይገልፃሉ። በተመሳሳይ መልኩ ክዋኔ ውበታዊ የሆነ የድርጊት ባህሪ፣ የንግግር ዘዴ፣ በአካል የሚከወን፣ በጊዜና በቦታ የተገደበ፣ በታወቀ መዋቅር በከዋኞች የሚቀርብ ከመሆኑም በተጨማሪ በተደጋጋሚ የሚፈፀም፣ በግልና በቡድን የሚዋቀር የማንነት ማሳያ እንደሆን

(Kapchan, 1995, 479) አስረድተዋል። በሌላ በኩል ደግሞ (Bronner, 1988,53) ክዋኔ የፎክሎርን ፅንሰ ሀሳብ የሚመራ ውበት ያለው ጥበባዊ ድርጊት ነው። ይኸውም የፎክሎር ጥበባዊ ድርጊት ከዋኝ፣ ቦታ፣ ተመልካች እና የክዋኔውን ሁኔታ የሚይዝ ነው በማለት አብራርተዋል።

በተጨማሪም (Finnegan, 1992, 95) የክዋኔ አይነቶችን የሚከወኑበትን ሁኔታ መሠረት በማድረግ የታቀዱ፣ ያልታቀዱ፣ ሰፊ ክብረ-በዓል ላይ ያሉ፣ ከሌሎች ጋር በሚደረጉ ኢ-መደበኛ ግንኙነቶች የሚፈጠሩ በማለት በአራት ከፍለዋቸዋል። የታቀዱ ክዋኔዎች ማህበረሰቡ ያዋቀራቸው ሲሆኑ ሰፊ ክብረ-በዓል ላይ ያሉ የክዋኔ አይነቶች ደግሞ ብዙ ህዝብ በሚገኝበት ቦታ የሚካሄዱ ናቸው። ያልታቀዱ ክዋኔዎች ማህበረሰቡ ሆን ብሎ ያላዋቀራቸው ቢሆኑም ራሳቸውን ግን ለክዋኔው ዝግጁ ያደርጋሉ። ከሌሎች ጋር በሚደረጉ ኢ-መደበኛ ግንኙነቶች የሚፈጠሩ ክዋኔዎች የታቀዱ ወይም ያልታቀዱ ሊሆኑ ይችላሉ። ከዚህም ክዋኔ ታስቦበትም ሆነ ሳይታሰብበት በማንኛውም አጋጣሚ ከታላላቅ (ታዋቂ) ከሆኑና ከተቀናበሩ ዝግጅቶች ጀምሮ እስከ ኢ-መደበኛ የሆኑ (በአጋጣሚ የሚፈጠሩ) ዝግጅቶች ድረስ የሚከወን መሆኑን መረዳት ይቻላል።

ስለዚህ ክዋኔ እንደየባህሉ አይነት የተለያየ አቀራረብ ይኖረዋል። በመሆኑም ክዋኔ የሚቀርብበትና የሚተረጎምበት ሁኔታ የተለያየ ነው። ይሁን እንጂ ዋናው ጉዳይ ፎክሎር ያለ ክዋኔ እንደማይገለጽና ህልውና ሊኖውም እንደማይችል (Finnegan 1977,101, Rappaport, 1992, 95) ይገልጻል።

በክዋኔ ተኮር አቀራረብ አንዱን ክዋኔ ለማጥናት/ለመረዳት የተለያዩ ነጥቦች ላይ ትኩረት ማድረግ ያስፈልጋል። እነዚህም ነጥቦች ከዋኙ፣ ተደራሲው፣ ለክዋኔው የሚቀርበው ጉዳይ፣ መቼቱ፣ መልዕክቱ፣ የአቀራረብ ቅደም ተከተሉ፣ ደንቡና የአድማጩ ምላሽ ዋነኞቹ ናቸው።

አንድን ክዋኔ ስንመረምር ቃላዊ ለሆኑና ቃላዊ ላልሆኑ ክዋኔዎች፣ ለመሳሪያው ቅንብር ለከዋኞቹ ድምፅና አጨዋወት ስልት፣ ለሚነሳው ርዕሰ ጉዳይ፣ ለፊት ገለፃዎች፣ ለባህላዊ ስምምነቶች፣ ለአካል እንቅስቃሴዎች (ማጨብጨብ፣ በጣት ማፏጨት.. ለአልባሳት፣ ለፀጉር አሰራር፣ ለጌጣጌጥ፣ ለሙዚቃ መሳሪያዎች፣ ለሀገርኛ ትዕምርቶች፣ በአጠቃላይ ከከዋኞቹና ከታዳሚዎቹ ለሚመጡ ክዋኔዎች ሁሉ ትኩረት መስጠት እንደሚያስፈልግ (Bauman, 1992, 44) ያስረዳሉ። ይህ ደግሞ በቃል ከሚነገሩት ክዋኔዎች በተጨማሪ ቃላዊ ያልሆኑትን

ማለትም እንደ ዳንስ ያሉ የሰውነት እንቅስቃሴዎች እና የፊት ገፅታዎች ያሉ ክዋኔዎች ዓላማ ምን እንደሆነ ለማወቅ ያስችላል።

በመሆኑም አንድን ክዋኔ ስንመረምር የክዋኔው አገላለፅና ጥበባዊ ተግባቦቱ መቼ፣ ከማን ጋር እና እንዴት ተከወነ የሚሉት ጥያቄዎች ይፈጠሩብናል። ስለዚህ ስለ ቴክስቱ፣ ከቴክስቱና ከአውዱ አንፃር የክዋኔውን ምንነት እና የሚያስገኘውን ማህበራዊ ፋይዳ መመርመር ያስፈልጋል። ከክዋኔ ፅንሰ ሀሳብ ተያይዘው የሚነሱ ጉዳዮች ውስጥ አውድ፣ ከዋኝና ታዳሚ ተጠቃሾች ናቸው። እነዚህን በዝርዝር እንመልከት።

### 2.2.1. 2.አውድ

በርካታ ምሁራን ስለ አውድ የተለያዩ ብያኔዎችን ሰጥተዋል። አውድ በፎክሎር ጥናት ውስጥ ከክዋኔ ጋር ተያይዞ የሚነሳ ዋና ጉዳይ ነው። አንድን ክዋኔ ስንመረምር አውድን ማዕከል ያደረገ መሆን አለበት። ይህም በሰዎች መካከል ያሉ ግንኙነቶችንና ባህላዊ ስምምነቶችን ለመረዳት ያስችላል። (Finnegan, 1992, 88) በመሆኑም አውድበቴክስት ላይ የሚያሳድረው ተፅዕኖ ከፍተኛ እንደሆነ ያመለክታል። ከዚሁ ጋር በተያያዘም (Dundes, 1986, 4)

The structure of performance events is a product of the interplay of numerous situational factors, including physical setting, participant's identities and roles, cultural ground rules for performance, norms of interaction and interpretation, and the sequence of actions, making up the conventional scenario of the event itself as a cultural scene.

በማለት አውድ የአንድን ክዋኔ አካላዊ መቼት፣ የተሳታፊዎቹ ማንነትና በክዋኔው ውስጥ የሚኖራቸውን ሚና፣ የድርጊት ቅደም ተከተል፣ ክዋኔውን የሚገዙት የተለያዩ ህግጋት እና በከዋኙና በታዳሚዎቹ መካከል ያለውን ተግባቦት አጠቃሎ እንደሚይዝ ይገልጻሉ። ከዚህም መረዳት የሚቻለው ፎክሎራዊ ክስተቶች የብዙ ሁኔታዊ አውድ ውጤቶች መሆናቸውን ነው።

አውድ በከዋኙ፣ በዋናው ጉዳይ ክዋኔና በታዳሚዎች ዙሪያ ያሉትን ጉዳዮች የሚገልጽ ነው። ለምሳሌ፡- የአንድን ቃል ግጥም ክዋኔ ብንመለከት ለግጥሙ፣ ለገጣሚው እና ለታዳሚዎቹ እንቅስቃሴ፣ ድርጊት፣ ሁኔታ እና ሌሎችም ትኩረት መስጠት ያስፈልጋል፡ ፡ አውድ ተኮር ምርምር ሲካሄድ ክዋኔው ከመጀመሩ በፊት ምን እናውቃለን፤ ከክዋኔ በኋላስ ምን አዲስ ነገር ተገኘ፤ ክዋኔው በሚከወንበት ወቅት የሚታዩ አካባቢያዊ ገለፃ እና በክዋኔ ጊዜ በተሳታፊዎቹና

በከዋኙ መሀል ያሉ ግንኙነቶች ምን ይመስላሉ? የሚሉትን ነጥቦች ማስተዋል አለብን (Finnegan, 1992, 95) ይላሉ። ይህን ማድረጋችን ደግሞ የሚከወነውን ቴክስት ከነሙሉ ፍቹ እንድንረዳ ያስችለናል።

(Bauman, 1982, 367) አውዳዊ ትንታኔን ስናደርግ ከግምት ውስጥ መግባት ያለባቸው ጉዳዮች ብለው ያስቀመጧቸው ስድስት ነጥቦች አሉ። እነሱም የፍቺ (የትርጉም) አውድ (የሚከወነው ዋና ጉዳይ ምንድነው?)፣ ተቋማዊ አውድ (የት ይወናል?)፣ ተግባቦዊ አውድ (ከሌላ የፎክሎር አይነት ጋር እንዴት ይዛመዳል?)፣ ማህበራዊ መሰረት (ምን አይነት ሰዎችን አካቷል)፣ ግለሰባዊ አውድ (ከግለሰቡ ኑሮ ጋር እንዴ ይስማማሉ?)፣ እና ሁኔታዊ አውድ (ማህበረሰቡ በምን ሁኔታ ውስጥ ነው የሚጠቀምባቸው?) የሚሉ ናቸው።

እነዚህን ክፍልፋዮች ባህላዊ አውድ እና ማህበራዊ አውድ በማለት በሁለት ጎራዎች መድበዋቸዋል። የኔም ጥናት የትኩረት ነጥብ የሚመሰረተው በእነዚሁ Bauman ባስቀመጣቸው ነጥቦች ላይ በመሆኑ ነጥቦቹን በአጭሩ እንመልከታቸው።

### ሀ.ባህላዊ አውድ

ባህላዊ አውድ ማህበረሰቡ ባለው ባህል መሠረት ለአንድ ቴክስት፣ ድርጊት ወይም ሁኔታ የሚሰጠው አውዳዊ ፍቺ ነው። ይህም ማለት የአንድ ቡድን ግንኙነት መግባቢያ ደንብ ሆኖ የሚያገለግል ነው። አውድ ለፎክሎሩ ባህሉ የሚሰጠውን ትርጓሜ ይመለከታል። በዚህ ስርም የትርጉም አውድ፣ ተቋማዊ አውድ እና ተግባቦታዊ አውድን እንደሚይዝ (Bauman 1982:363) ይገልጻል።

### ለ.የትርጉም አውድ

የትርጉም አውድየፎክሎሩን ባህላዊ ትርጉም ለመረዳትና ለማወቅ ወሳኝ ነው። ይህም ማለት ባህሉ ፎክሎራዊ ጉዳዩን የሚተረጉምበትን አንፃር ለማወቅ ያስችላል ማለት ነው። ከዚህም በተጨማሪ ፎክሎራዊ ጉዳዩ በባህሉ ባለቤቶች በምን መልኩ እንደተወከለ፣ እንዴት እንደሚተላለፍና ምን ምን እሴቶች እንደተወከሉበት ይመረምራል። በፎክሎሩ ውስጥ የሚገኙትን የአከዋወን ስልቶች፣ መንስኤና ውጤት እንዲሁም ትምህርታዊና ዘይቤያዊ አገላለጾች እንዴት እንደተገለጹበት ትኩረት ይሰጣል። ፎክሎረኞች ባህላዊ ትርጉምን ከባህሉ ባለቤቶች በቀጥታ ቢወስዱ ጥናታቸው የተሻለና ትክክለኛ እንደሚሆን ዝኒ ከማሁ ያስረዳሉ።

**ሐ.ተቋማዊ አውድ**

ተቋማዊ አውድ ፎክሎራዊ ጉዳዩ የት ቦታ ይከወናል? የሚለውን ጥያቄ የሚመልስ ሲሆን ጉዳዩ የሚከወንበት ተቋም ፖለቲካዊ፣ ማህበራዊ ወይስ ሃይማኖታዊ መሆኑን ከመመርመር ባሻገር ምን አይነት ተቋማዊ ፋይዳ ያበረክታል የሚለውን ይመለከታል። በዚህ አውድ ፎክሎራዊ ጉዳዩ በተለያዩ ተቋማት ውስጥ ያለውን አውድ ይመለከታል። ይህን ሲያደርግ ተቋማቱና ፎክሎራዊ ጉዳዩ በምን እንደሚገናኙ መመርመር፣ ተቋማቱ በየትኛው ባህል ውስጥ እንደሚገኙና እንዴት እንደሚያገለግሉም ማተኮር አስፈላጊ እንደሆነ ዝኒ ከማሁ ያስረዳሉ።

**መ.ተግባቦታዊ አውድ** በክዋኔው ውስጥ በፎክሎራዊ ጉዳዮች መካከል ያለውን ዝምድና ይመለከታል። ይህም ማለት በአንድ ክብረ በዓል ወቅት ከበዓሉ ጋር ተያይዞ ልብሱ፣ ድግሱ፣ ዘፈኑ፣ ጭፈራው… አብሮ ይመጣል። ለምሳሌ፡- የዚህ ጥናት ትኩረት አቅጣጫየሆነውን የገፈራ ከበራን ስንመለከት ስርዓቱን ራሱን ችሎ ለማጥናት ተያይዘው የሚመጡትን፡ ቃላዊ ግጥሞች ልዩ ልዩ ቁሳዊ ባህሎችና ቃል ግጥሞቹ ከገፈራው ክዋኔ ጋር ተያይዞ የሚመጡ እንቅስቃሴዎችን ማጥናት (መዳሰስ) ያስፈልጋል ማለት ነው።

**ሰ.ማህበራዊ አውድ**

ይህ አውድ ከቤተሰብ አባላት ባልና ሚስት፣ ልጆች ጀምሮ፣ እስከ ቡድናዊ፣ ሃይማኖታዊ ቡድኖች፣ አካባቢያዊና የመሳሰሉትን ተግባቦት የሚያጠቃልል ነው። ማህበሩ (Folk group) የሚገናኙበት ነው። በመሆኑም ከዋኙ፣ ተመልካች ወይም ተሳታፊ በጋራ ይገናኙበታል። ማህበራዊ አውድ ማህበራዊ መሠረት፣ ግለሰባዊ አውድ እና ሁኔታዊ አውድ የተሰኙ ሶስት መልኮች አሉት። እነዚህን ቀጥሎ እንመለከታለን።

ማህበራዊ መሠረት የማህበራዊ ግንኙነት አውድ በክዋኔ ላይ ትልቅ ተፅእኖ አለው። አንድ ፎክሎራዊ ቴክስት የሚከወነው እንደ ማህበረሰቡ የስልጣን ደረጃ የክብር ተዋረድ ሊወሰን ይችላል። አንድ ቀልድ፣ ታሪክ፣ ሚስጥር ወይም ስነቃል በሚከወንበት ወቅት እንደ ማህበረሰቡ የአመለካከት ሁኔታ ይወሰናል። እያንዳንዱ ማህበረሰብ የራሱ የሆነ የእድሜና የስልጣን ተዋረድ አለው። ስለዚህ ይህ አውድ ትኩረቱ ከፎክሎሩ ባለቤቶች ማንነት ጋር ተያይዞ የሚመጣውን አውድ ያጤናል ማለት ነው።

ክዋኔ በጾታ፣ በእድሜ በቡድን ይለያያል። ስለዚህ ክዋኔውን ማህበረሰቡ የሚጋራው ቢሆንም ክዋኔው ሁሉንም ማህበረሰብ አይወስንም ማለት ይቻላል። ስለዚህ የፎክሎሩን አውድ ለመረዳት የፎክሎሩን ባለቤቶች ማንነት (ፎክ ቡድን) ማወቅ ግድ ይላል።

ግለሰባዊ አውድ ግለሰቡ በፎክሎራዊ ጉዳዩ የሚኖረው ሚና፣ ፎክሎሩ ለግለሰቡ የሚሰጠው ፋይዳ፣ ግለሰቡ ለፎክሎሩ የሚሰጠው ትርጉም እንዲሁም ግለሰቡ ከሌሎች ግለሰቦች ጋር በመዋቀር ቡድን የመሰረተበትን አውድ ያጠናል።

ሁኔታዊ አውድ አንድ ፎክሎራዊ ጉዳይ የተደራጀ፣ ፍሰታዊና የተለመደ አከዋወን ወይም አውድ ሊኖር ይችላል። ይሁን እንጂ አንዳንድ ጊዜ ድንገተኛ ለውጥ የሚፈጥሩ ሁኔታዎች ሊከሰቱ ይችላሉ። እነዚህ ሁኔታዎች የሚከሰቱትም ከፎክሎራዊ ጉዳዩ፣ ካለው ነባራዊ ሁኔታ፣ ለመከወን ከምንጠቀምበት ስልት እና ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊ ለውጥ ሊሆን ይችላል። ለምሳሌ፡- አንድ ፎክሎራዊ የቃልግጥም ቴክስት ለመከወን እንደየ ማህበረሰቡ የአኗኗር ሁኔታ፣ ባህልና አካባቢ ሁኔታ ተጽእኖ ይኖረዋል።

ቴክስቱም ሲከወን በከዋኙና በተሳታፊዎቹ መካከል እንዲሁም በተመልካቹ መካከል ባለው ማህበራዊ አውድ ይወሰናል።

አጥኚው ሁኔታዊ አውድን ለማግኘት ራሱንም ሆነ ቡድኑን መጠየቅ ያለበት እየተከናወነ ያለው የፎክሎር ቅንጣት አሁን ባለው ሁኔታ ውስጥ ምን ማለት ነው? ብሎ በመጠየቅ ለቡድኑ ተግባቦት እንዴት እንደሚውል ማጣራት ላይ ነው።

በአጠቃላይ ከላይ ከተጠቀሱት ሀሳቦች እንደምንረዳው አንድን ክዋኔ ለመከወን የራሱ የሆነ አውድ እንደሚያስፈልገው ነው። በአውድ ውስጥ የሚገኙት እንደ ተሳታፊ፣ ከዋኝ፣ መቼት ያሉት ደግሞ ለእያንዳንዱ ክዋኔ የራሳቸው አስተዋጽኦ አላቸው።

## 2.2.1. 3.ከዋኝ

ክዋኔ አንድ ድርጊት በተፈጸመበት ጊዜ ያለውን ነገር የሚገልጽ ነው። በዚህ ባለው ነገር ላይ በመመርኮዝም የከዋኞቹን ሚና ምን እንደሆነ መመርመር ያስፈልጋል። በመሆኑም ከዋኞቹ ያደጉበትን ማህበረሰብ ባህል፣ ወግና ልማድ በማሳየት በአቀራረቡ ነፍስ ይዘሩበታል። ይህንን ጉዳይ አስመልክተው (Bauman, 1992, 44) "The performer assumes responsibility to an audience for a display of communicative skill and effectiveness of the

performer's accomplishment." ይህን በማለትም ከዋኞቹ ክዋኔውን የተሳካ ከማድረግም በተጨማሪ ታዳሚዎችን የማግባባት ኃላፊነት አለባቸው ተብሎ እንደሚታሰብ ይገልጻሉ።

(Finnegan, 1992, 90-91) ከዋኞች ከፍተኛ አድናቆት የተሰጣቸው፣ ከታዳሚው የተለየ ተሳትፎ የሌላቸው እና በእነዚህ በሁለቱ መካከል ያሉ ናቸው በማለት በሶስት ከፍለዋቸዋል። በሌላ መልኩ ደግሞ (Bauman, 1992, 48) ክዋኔ በሚከወንበት ጊዜ ለከዋኞቹ ድርጊት፣ ለሚከውኑበት እቃ እና ለሚያሳዩት ሚና ከተመለከትነው ክዋኔ በመነሳት ትርጉም የምንሰጥበት ነው ይላሉ። ይህም የሚያመለክተው በክዋኔ ውስጥ ለአጠቃላይ የከዋኞቹ ሁኔታ ትኩረት መስጠት አስፈላጊ መሆኑን ነው።

ከዋኞቹ የሚያነሷቸው ርዕሰ ጉዳዮችን የሚከውኗቸው ክዋኔዎች ማንነታቸውን በመግለጽ ረገድ የራሳቸው የሆነ አስተዋጽኦ ያበረክታሉ (Bronner, 1988, 53):: ስለሆነም ከዋኞች ለክዋኔ ያላቸው ስሜትና ተሳትፎ እስከምን ድረስ እንደሆነ፤የሚጠበቅባቸውን ሚና በተገቢው መልኩ እየተወጡ እንደሆነና ክዋኔውን እየከወኑ ወይም ከመከወናቸው በፊት የፈጠራ ችሎታቸው ምን ያህል እንደነበር መጤን አለበት።

አንድ ክዋኔ ሲከወን የታዳሚዎቹ ሁኔታ ቴክስቱ ላይ ተጽዕኖ እንደሚያሳድር ሁሉ የከዋኞቹ ማንነትም በታዳሚዎቹ ማህበራዊ ደረጃ ይወሰናል (Dundes, 1986, 28):: ስለሆነም አንድ የፎክሎር ምርምር ሲደረግ የከዋኞች እድሜ፣ ፆታ፣ ማህበራዊ ደረጃ፣ ልምድ፣ ብቃትና ተቀባይነት ግምት ውስጥ መግባት አለበት።

የክዋኔን ዋና ቦታ የሚይዘው ከዋኙ ነው። ምክንያቱም የከዋኙ ሚና የሌሎችንም ሰዎች ቀልብ ስለሚስብ ነው። ስለዚህ ቀዳሚው ከዋኙ ሲሆን ሁለተኞቹ ደግሞ ታዳሚዎች ናቸው። አንዳንድ ጊዜ የተሳታፊዎች ተሳትፎ ላቅ ያለ ሲሆን ተሳታፊዎቹን ከከዋኞቹ መለየት በጣም ያስቸግራል። ይህም ከከዋኙ ቀጥሎ ትልቁን ቦታ የሚይዘው ተሳታፊው እንደሆነ ያመለክታል።

### 2.2.1. 4.ታዳሚ

ከአውድና ከከዋኝ በመቀጠል ክዋኔ ሲነሳ ተያይዞ የሚመጣው ጉዳይ ታዳሚ ነው። አንድ ክዋኔ ሲከወን በአጋጣሚ ወይም ደግሞ ሆን ተብሎ የሚገኙ ሰዎች ታዳሚዎች ይባላሉ፡ ፡ እነዚህም ሰዎች ክዋኔው ላይ ወይም በቀጣይነት ይሳተፋሉ፤ አልያም ደግሞ ለተወሰነ ጊዜ ብቻ ይቆያሉ። ክዋኔን ያለ ተሳታፊ ማሰብ አስቸጋሪ ነው፤ ምክንያቱም የተሳታፊዎቹ ሁኔታ በራሱ ክዋኔውን ማስቀጠል ስለሚችል ነው።

አንድ ክዋኔ በሚከወን ጊዜ ክዋኔው ለሚካሄድበት መቼት፣ ለተሳታፊዎቹ ባህሪያትና ምላሽ ትኩረት መስጠት ያሻል። ይህ ደግሞ አዲስ አቅጣጫን ያስጨብጣል። በመቼቱና በተሳታፊው መካከል ያለው ግንኙነት እንደ ተሳታፊዎቹ እድሜ፣ ጾታና ማህበራዊ ደረጃ ይወሰናል። ተሳታፊዎቹ በራሳቸው መንገድ ክዋኔውን ሊረዱት ይገባል። ከክዋኔ በኋላ ታዳሚው የሚሰጠው ምላሽ አዎንታዊ ወይም አሉታዊ ከሆነ አድናቆቱን አልያም ስሜቱን እየገለጸ ነው ለማለት ይቻላል። ስለዚህ የፎክሎር ጥናት ተመራማሪ ታዳሚዎቹ በክዋኔው ተሳታፊ መሆናቸው፣ ተሳትፎአቸው እንዴት እንደነበርና ወደ ክዋኔው ከመግባታቸው በፊት ከነበራቸው ሁኔታ እንዴት ሊነጠሉና በክዋኔው ሊመሰጡ እንደቻሉ መመርመር አለበት።

(Finnegan, 1992, 91-92) በክዋኔ ጊዜ በከዋኝና በታዳሚ መካከል ግልጽ የሆነ ልዩነት አለ። ታዳሚዎች መደበኛ የሆነ ድርሻ የላቸውም። ስሜታቸው እንዳዘዛቸው ምላሽ ይሰጣሉ፤ የማይሳተፉም አሉ። ያም ሆነ ይህ ግን የራሳቸውን ተጽዕኖ ያሳድራሉ፤ በማለት የታዳሚዎች ምላሽ መስጠትም ሆነ አለመስጠት በክዋኔው ላይ ተጽዕኖ እንደሚያሳድር ይገልጻሉ። በመሆኑም በክዋኔ ውስጥ ታዳሚዎቹ ለሚያሳዩት ማንኛውም እንቅስቃሴ ትኩረት መስጠት ያሻል።

### 2.2.1. 5.ቴክስት

ቴክስት የሚለው ቃል ከዕሁፋዊ እሳቤው ባሻገር ቁሳዊ ነገሮችን እንደሚያመለክት እና ቃላትን፣ ቁሶችን፣ ሀሳብን እና ባህሪን የሚጠቁም መሆኑን (Sim እና Stephen ፣ 2005, 19) ያስረዳሉ።

በተጨማሪም ክዋኔ፣ ቃላዊ ትርክቶች እና ሃይማኖታዊ ክብረ-በዓላትም ቴክስት መሆናቸውን ይገልፃሉ። በዚህ ጥናትም በዋናነት ትኩረት የሚደረግባቸው ቴክስቶች "የገፈራ ክዋኔ"፣ በገፈራው ክዋኔ ወቅት የሚባሉ ቃል ግጥሞች፣ "የክዋኔው ተሳታፊዎች የሚጠቀሙባቸው ቁሳቁስና አልባሳት፣ ምግቦች፣ ድርጊቶች… ናቸው።

## 2.3.ከበራ

ስለ ከበራ ምንነት የተለያዩ ምሁራን ተመሳሳይ አንድምታ ያላቸው የተለያዩ ምላሾችን ሰጥተዋል። ከነዚህም መካከል Sims እና Stephen (2005፣95) ሲገልጹ በማህበረሰቡ ዘንድ ተደጋጋሚ (repeated) ሆኖ የሚከበር፣ የተለመደ ድርጊት የሚስተዋልበትና ዘወትር ከምንከውናቸው ልማዶች የተለየ ዓላማ ያለው መሆኑን ሲገልጹና፤ በፎክሎር ጥናት ውስጥ

ያለውን ቦታ ሲያስረዱን፤ ከበራ አንድ ልዩ ትውፊት አይነት ሆኖ ፎክለሪስቶች ሲያጠኑት ግን የተለያየ ምድብ ውስጥ ያስገቡታል። ከበራዎች የሚደጋገሙ ቢሆኑም ከልማድ የበለጠ አላማ ያላቸውና የተደራጁ ሲሆኑ አልፎ አልፎ የአንድን ቡድን አባላት ያስተዋውቃሉ። ብዙዎቹ ከበራዎች በአንድ ላይ ሲሆኑ የተለያዩ የፎክሎር አይነቶችንይፈጥራሉ። ለምሳሌ እንደ ቃላዊ ግጥሞች፣ዜማዎችና እንጉርጉሮዎች ያሉ ቃላዊ ፎክሎሮችን፣ እንደ የአካል እንቅስቃሴ፣ውዝዋዜ ያሉ ልማዳዊ ፎክለሮችን እና እንደምግብ፣መፅሀፍት፣ሽልማቶች፣ልብሶች ያሉ ቁሳዊ ፎክሎሮችን እንደሚይዙ ምሁራን እንደሚከተለው ይገልፃሉ።

A ritual is a particular type of tradition that many folklorists study as a distinct category of folklore. Rituals are repeated, habitual actions, but they are more purpesful than custom, rituals are frequently highly organized and controlled, often meant to indicate or announce membership in a group. Most rituals bring together many types of folklore. Verbal, such as chants, recitations, poems or songs, customary such as gestures, dance or movements, and material, such as food, books, awards, clothing. (Sims & Stephen: 2005: 104)

በሌላ በኩል ደግሞ እንደ Rappaport (1992፣157) አገላለጽ ከበራ ከአብዛኞቹ የመግባቢያ አይነቶች አንዱ ሲሆን ለሌሎች (በቋንቋ ጭምር ለማይገለጹት) ተግባቦቶች መነሻ የሆነ፤ ግልጽ የሆነ ቅርጽ ያለው፤ የተለያዩ ገጽታዎችና ባህሪያት ያሉት ከመሆኑም በላይ እነዚህ ባህሪያቶቹ አነሰም በዛም እርስ በእርስ የተያያዙ መሆናቸውን ይገልጻሉ።

ከዚህም በተጨማሪ እያንዳንዱ ማህበረሰብ በሚኖርበት አካባቢ በዝግጅትና በጉትት የሚጠብቃቸው ከበራዎች አሉት። እነዚህ ከበራዎች ደግሞ ወቅታዊ፣ ማህበራዊ እና ሃይማኖታዊ በሚል የሚታወቁ ናቸው:: (Sims እና Stephen፣ 2005፣102-105) እንደሚያስረዱት ከበራዎች ሃይማኖታዊ ይዘት ያላቸውና እና ከሃይማኖታዊ ይዘት ውጭ መሆናቸውን ይገልጹና አንዳንዶቹ ከበራዎች ደግሞ ሁለቱንም የሚይዙ መሆናቸውን ያስረዳሉ።

ከዚህም በተጨማሪ አብዛኞቹ ከበራዎች ሲከበሩ በተመሳሳይ ጊዜ በርካታ ፎክሎራዊ ጉዳዮችን በአንድ አጠቃላይ ይዘው ይመጣሉ። ለምሳሌ፡-የዚህ ጥናት ትኩረት አቅጣጫ የሆነውን የገፈራ

ስርዓተ ክዋኔን ስንመለከት ከበራውን ራሱን ችሎ ለማጥናት ተያይዘው የሚመጡትን ቃላዊ ግጥሞች፣ ልዩ ልዩ ቁሳዊ ባህሎችና ቃል ግጥሞቹ ክዋኔ ጋር ተያይዞ የሚመጡ እንቅስቃሴዎችን ማጥናት (መዳሰስ) ያስፈልጋል ማለት ነው። ይህንንም በተመለከተ (Sims እና Stephens፣ 2005፣95) እንደሚከተለው ገልጸውታል፡

Rituals are frequently highly organized and controlled, often meant to indicate or announce membership in a group. Most rituals bring together many types of folklore: verbal, such as chants, recitations, poems or songs; customary, such as gestures, dance or movements; and material, such as food, books, awards, clothing and consumes....

አንድ ፎክለሪስት አውዱን መነሻ በማድረግ በሚያጠናበት ወቅት ይዘትን መግለጽ ባቻ ሳይሆን በዙሪያው ያሉ ቁሳሶች፣ ጌጣጌጦች፣ ስዕሎች፣ ምልክቶች እርስ በርስ ምንግንኙነት አላቸው? በትርጉሙስ ላይ የሚያመጡት ነገር አለ?" በሚሉት መሰረታዊ ጥያቄዎች ላይ መመስረት እንዳለበት (Finnegan ፣1992፣86) ገልጸዋል።

ከበራ በተግባር የሚገለፅ አንድ የፎክሎር ዘርፍ ነው። በከበራዎች ላይ እያንዳንዱ የፎክሎር ዘርፍ ሊስተዋል ይችላል። ከበራ በስነ ቃሎች፣ በቁሶችና በተለያዩ ልማዶች ታጅቦ ይከናወናል። ይህ ከበራም ፎክቡድኖች ወይም ማህበረሰቦች የሚያውቁትና የሚተገብሩት የራሱ ስርዓት እንዳለው (Sims እና Stephen ፣2005፣158) ገልጸዋል።

አንድ ህብረተሰብ በህይወቱ ውስጥ ተደጋግመው ለሚደረጉ ከበራዎች መነሻ ምንነት የሚያምንበትን ነገር ወይም ሃይማኖቱን ይጠራል። ከሃይማኖቱ ጋር አጣምሮ ይመለከታቸዋል። ህብረተሰቡ ደስታውን፣ ሀዘኑን፣ ጭንቀቱን፣ ብሶቱን፣ ማንነቱንና ሌሎችንም ለመግለጽ ከበራዎችን እንደ አጋጣሚ ይጠቀማቸዋል። በህይወቱ ውስጥ የሚጠቀምባቸውንና የሚመራባቸውን እሴቶችና ተምሳሌቶችን መግለጫ አድርጎም ይወስዳቸዋል።

### 2.3.1.የከበራ ባህሪያት

ከበራዎች በምንም ምክንያት ይከበሩ ክዋኔ አላቸው። ከዚህ ጋር በተያያዘም የክዋኔና የከበራ ትስስርን በተመለከተ ከበራ ከሌለ ክዋኔ እንደማይኖርና ክዋኔ በራሱ ግልጽ የሆነ መልዕክት ያለው ድርጊት መገለጫው እንደሆነ (Rappaport, 1992, 25) "...There is no performance, there is no ritual, performance it self is an aspect of that which is performed the medium is a part of the message, more precisely, it is a meta message about what ever is encoded in the ritual." በማለት ያስቀምጣሉ። በመሆኑም ከበራ በየትኛውም ህብረተሰብ ይከወን አብዛኛውን ጊዜ እነዚህ ባህሪያት ይስተዋሉበታል (Salmon፣ 2004፣321) ።

1. ***መዋቅራዊነት፡-*** ይህ የከበራ ባህሪ የከበራው ክዋኔ ከተጀመረበት አንስቶ እስከሚጠናቀቅ ድረስ የሚያልፍባቸውን ደንቦችና አደረጃጀቶች የሚመለከት ነው። የትኛውም ከበራ በምንም ምክንያት ቢከበር የራሱ የሆነ የሚከተለው መዋቅርና ደንብ አለው። እያዳንዱ የከበራ እንቅስቃሴም የከበራው ባለቤት ባበጀውና በሚመራበት ደንብ መሰረት ይመራል።

2. **ቅደም ተከተላዊነት፡-** ይህ ባህሪ በክዋኔ ወቅት የሚቀርቡ ድርጊቶች ወይም ሁነቶች የሚከወኑበትን ቅደም ተከተል የሚያሳይ ነው። በከበራ ወቅት ቀድሞ የሚመጣ ቀጥሎ የሚመጣ መጨረሻ የሚመጣ እየተባለ ክዋኔዎች በእለፍ ተቀደም ይቀርባሉ። በመዋቅር ያሉ ደንቦች የተለመዱ በመሆናቸው ሳይዛነፍ ቅደም ተከተላቸውን ጠብቀው ይቀርባሉ።

3. ***ተደጋጋሚነት፡-*** ይህ ባህሪ የጊዜንና የጉዳዩን ድግግሞሽ የሚያሳይ ነው። ከበራዎች በሳምንት በወር ወይም በአመት ተደጋግመው ሊመጡ ይችላሉ። በሌላ በኩል ደግሞ በአንድ ከበራ ላይ የሚታዩ ክዋኔዎች ያ ከበራ ተመልሶ በሚመጣበት ጊዜም ተደጋግመው የሚቀርቡ ናቸው።

4. ***ታዳሚ፡-*** ከበራ ለመከበር ወይም ለመከወን ተሳታፊ ብቻ ሳይሆን የግድ ታዳሚም ያስፈልጋል። በመሆኑም በአድማጭና ተመልካች ፊት ይከወናል።

5. **ውጤት፡-** ይህ ደግሞ ከበራ ለባለቤቱ የሚሰጠውን ጠቀሜታ የሚመለከት ጉዳይ ነው። ከበራው ከተከናወነ በኋላ ለከዋኙ ህብረተሰብ ስነ-ልቦናም ሆነ ሌላ የሚሰጠው ፋይዳ ወይም ውጤት ይኖረዋል።

6. ቅዱሳዊነት፡- አብዛኞቹ ከበራዎች በሚያከብራቸው ማህበረሰብ ዘንድ ቅድስናን ወይም ንፁህነትን ያመጣሉ ተብሎ ይታሰባል። ማህበረሰብ ከበራዎችን በማድረጉ ከርክሰት እንደሚፀዳ ይሰማዋል። አንዳንዴም ካለበት ዝቅ ያለ ደረጃ ከፍ ወዳለ ደረጃ የመሸጋገሪያ መገለጫዎች ሆነው ያገለግላሉ።

## 2.4.ሀገረሰባዊ አስተዳደር

ሀገረሰባዊ አስተዳደርን በተመለከተ ሙሁራን በርካታ ብያኔ ይሰጣሉ።ከሙሁራን መካከል Nsarkoh ተጠቃሽነው። Nsarkoh ሀገረሰባዊ አስተዳደር ከማዕከላዊ መንግስት አስቀድሞ የነበረ፣በልማዳዊ ህግና በአካባቢያዊ ደንብ የሚመራ ሰርአት ነው በማለ ትጽፏል።(Nsarkoh 1964:13)(Cowan 1995:4-5) የተባለው ፀሀፊ ደግሞ የአፍርካ ህዝቦች ሀገር በቀል የአስተዳደር ስርአቶች የሚጋሯቸው ባህሪያት እንዳሏቸው ያስረዳል።ከነዚህ መለያ ባህሪያት መካከል አንዱ በሀገረሰባዊ ንጉሥ ወይ በባለአባት የሚመሩ መሆናቸውን ይጠቅሳል።

አሜሪካናታላቋ ቢሪታኒያም ሀገረሰባዊ የአስተዳደር ሰርአትን በተመለከተ የራሳቸውን አመለካከት ናግምት አላቸው።አሜሪካዊያን ለሀገረሰባዊ አስተዳደር ያላቸው አመለካከትና ግምት ላቅ ያለ ነው።ለዚህ በጎ አመለካከት መሰረታዊ ምንጩ ደግሞ "The less government the better" የሚለውና ረዥም ዘመናትን ያስቆጠረው የሀገሪቱ መሰረታዊ መርህ ነው።ለታላቋ ቢሪታኒያ ደግሞ ሀገረሰባዊ የአስተዳደር ሰርአት እንደአንድ ታላቅ የፖለቲካ ትምህርት ቤት፣የአኗኗር እና የባህርይ መገለጫ ተቋም ተደርጎ ነው የሚቆጠረው (Nsarkoh 1964:13)።

እነዚህ ቀደምት አባታዊ የአስተዳደር ስርአቶች (Paternal government)ጊዜውያለፈባቸው፣የተረሱና ለመጪዎቹ ስርአቶች የሚያበረክቱት አንዳች ፋይዳ የሌላቸው እንደሆኑ አድርጎ የጻሀፊም አለ።በጸሀፊው እምነት ሀገረሰባዊ አስተዳደር ውስጥ በከፍተኛ የአመራር ቦታ ላይ ያሉ ሹማምንት በሙስና የተዘፈቁ፣ለቦታው ብቃት የሌላቸውናተገቢ ያልሆኑ ሰዎች ናቸው።በመሆኑም ይህ ሀገረሰባዊ የአስተዳደር ሰርአት እንደነዚህ ዓይነቶቹ አላስፈላጊ ሰዎች በስልጣናቸው እስከ ወዲያኛው እንዲቆዩና ስልጣናቸውን ቀጣይነትና ዘላቂነት እንዲኖረው የሚያደርግ፣የከፉ ሰርአት ተምሳሌትነው።(Wraith 1953:33)

በሌላ ወገን ደግሞ Sklar(1999:117-118) እና Bahru(2006:18) ሀገረሰባዊ የፖለቲካ ስርአት ጊዜ ያለፈባቸውና ረብ የለሽ ሳይሆን ዛሬም ድርስ በበርካታ ወገኖች የሚፈለግ፣ቀደም ሲልም ለዘመናዊ የአስተዳደር ሰርአት መሰረት የሆነ መሆኑ በመጥቀስ የwraithንሀሳብ ያጣጥሉታል።ለዚህ ለመከራከሪያ ሀሳባቸውም የተለያዩ የአፍርካ ውስጥ የተካሄዱት የፀረ ቅኝ አገዛዝ ትግሎችና ንቅናቄዎች፣በእነርሱም የተገኙ ውጤቶች፣በሀገረሰባዊ የፖለቲካ ሰርአት የታገዙ ነበሩ።ከነፃነት በኃላም ቢሆን ከበፊቱ ባልተሻለ ወታደራዊ አገዛዝ ስር የወደቀና በሙስና የተዘፈቁ የአፍርካ ሀገሮች፣ከዚህ ከብልሹ ሰርአት ለመላቀቅ ብሎም አዲስ የዲሞክራሲ ሰርአት ለመገንባት ሲሉ ወደኃላቸው ተመልሰው ከቅኝ የአገዛዝ ሰርአት በፊት የነበረውን ሀገረሰባዊ የፖለቲካ ስርአታቸውን መልሰው ለማደስና በስራ ላይ ለማዋል ተገደው እንደ ነበር እነዚሁ ፀሐፍትያትታሉ።

የምዕራብ አፍርካን ሀገረሰባዊ የአስተዳደር ሰርአትያጠኑት Fortes እና Earus (1940) የምዕራብ አፍርካ ሀገረሰባዊ የአስተዳደር ስርአቶች ሶስት ገጽታዎች እንዳሏቸው እንዲህ ሲሉገልፀዋል:-Cowan(1995:4-5) የተባለው ፀሀፊ ደግሞ የአፍርካ ህዝቦች ሀገር በቀል የአስተዳደር ስርአቶች የሚጋሯቸው ባህሪያት እንዳሏቸው ያስረዳል።ከነዚህ መለያ ባህሪያት መካከል አንዱ በሀገረሰባዊ ንጉሥ ወይ በባለአባት የሚመሩ መሆናቸውንይጠቅሳል።

ሀገረሰባዊ የአስተዳደር ሰርአት ከሁሉም በላይ የሚተገበረው በአንድ በተወሰነ አከባቢ በሰፈረና በግብርናሥራ በሚተዳደር ማህበረሰብ ዘንድ ነው።በእንደዚህ ዓይነቱ ማህበረሰብ ዘንድ የሚተገበረው ሀገረሰባዊ የፖለቲካ ሰርአት በአንጻራዊ መልኩ በሚገባ የተጠናከረና የተደራጀ ነው።በነዚህ ህዝቦች ዘንድ ሀገረሰባዊ መሪው ህዝቡን በችግርና በአደጋ ወቅት የሚመራ ብቻ ሳይሆን፣ከሌሎች ረዳቶቹና አማካሪዎቹ ጋር በመሆን የሚያስተዳድር፣የሚዳኝ፣የህዝቢን ሀብትና ደህንነት የሚጠብቅ ፖሊሲ የሚያዘጋጅና እያንዳንዱን የማህበረሰቡ በበላይነት የሚመራ መሪ በመሆንያገለግላል (Harris ,1957,5፣Cowan,1995፣5)።

ወደ ኢትዮጵያ ስንመጣ፣ከፍ ብለው ከተጠቀሱትጋር በብዙ መልክ የሚመሳሰሉ ሀገረሰባዊ የፖለቲካ እና ውሳኔ አሰጣጥ ስርአቶች በጉራጌ፣በሲዳማ፣በካምባታ ...ወዘተ ህዝቦች ዘንድ ይተግበር እንደነበር (Bahru1 17,Yakob,45;Aadland, 29;2006) ይገልጻሉ።

# ምዕራፍሶስት

## የአጠናንዘዴ

ይህ ጥናት ዓይነታዊ (Qualitative) ሲሆን የጥናቱን አላማዎች ለማሳካትና የምርምር ጥያቄዎችን ለመመለስ ያስችል ዘንድ መረጃዎች ከቀዳማይና ከካልአይ የመረጃ ምንጮች ተሰብሰቧል።ዓይነታዊ ምርምር ሂደት ሁሉም ነገሮች በቁጥር የሚገለጡ ወይም የሚወከሉ አይደሉም።ተመራማሪዉ ለማጥናት የፈለገዉ ጉዳይ በመጠን ሳይሆን በዓይነት የሚገልፅ ይሆናል።ስለዚህ … መረጃዎቹን ተንትኖ የጥናቱን ዉጤት የሚያቀርበዉትረካዊ ወይም ገለጣዊ መንገድን ተከትሎ ነዉ። (ያለዉእንዳወቀ2009፡20-21)

አንድ አጥኚ ወደ መስክ ከመሄዱ በፊት ለመስክ ሥራው መሰረት የሚሆን መረጃን በማግኘትና በማንበብ የመስክ ሥራውን አቅጣጫ ማስያዝ እንዳለበት(Goldstein 1964፡37) ይገልጻሉ።በመሆኑም ካልአይ መረጃን ለማሰባሰብ ስለአካባቢው የተጻፉ የተለያዩ ሰነዶች ፍተሻተደረጋል።ሰነዶቹ ከክልል፣ከዞንና ወረዳ መንግስት ኮሚኒኬሽን ቢሮዎች እና ከጉዳዩ ቅርበት አላቸዉ ተብሎ ከሚታመንባቸዉ ግለሰዎች ለማግኘት ጥረት ተደረጓል።ቀዳማይ መረጃዎች ደግሞ ከመስክ በምልከታ፣በቃለ መጠይቅ እና በተተኳሪ ቡድን ውይይት የተገኙ ጥሬ መረጃዎች ናቸው።

### 3.1 ምልከታ

ለፎክሎር ጥናት ከመስክ መረጃ ከሚሰበሰብባቸው ዘዴዎች መካከከል ዋናውና ቀዳሚው ምልከታ ነው።ምክንያቱም አብዛኛው የፎክሎር ጥናት ከመስክ በሚሰበሰብ ተፈጥሮአዊ ዐውድ የሚሰበሰቡ መረጃዎችን የሚፈልግና ምልከታ የግድ የሚሆንበት አጋጣሚው ብዙ ነው።ምልከታ በዓይን ብቻ የሚታይ ሳይሆን ከሁሉም የስሜት ህዋሳቶቻችን ጋር ህብረት በመፍጠር የተሟላ መረጃ የሚገኝበት ዓይነተኛ ስልት ነው (Goldstein .1964:77)።

በዚህም መሰረት የባህላዊ አስተዳደር ስርዓተ ክዋኔ ለመረዳት የምልከታ (Observation) ዘዴን አጥኚው ተጠቅሟል።

ምልከታውም ኢ- ተሳታፊ በሆነ መልኩ ተካሂዷል።ይህም የሚሆንበት ምክንያት በክዋኔው ላይ የሚከወኑ ድርጊቶችን ሙሉበ ሙሉ ለመከታተል እንዲያመች በማሰብ ነው።ይህን

ዘዴ በመጠቀም በማህበረሰቡ የባህላዊ አስተዳደር ሰርአት ክዋኔ በሚደረግበት ጊዜና ቦታ በመገኘት የድምጽ ሪከርድና ቪዲዮ ካሜራን በመጠቀም ከተፈጥሯዊው መቼት አንፃር መረጃዎች ተሰብስቧል።

## 3.2 ቃለ መጠይቅ

ይህ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ በምልከታ ወቅት የሚሰበሰቡ መረጃዎችን መነሻ በማድረግ በምልከታ ወቅት ከቁጥጥር ውጭ ሆነው ያመለጡ መረጃዎችን ለመጨመር፤በምልከታ የተሰበሰቡት መረጃዎች ላይ ከባህሉ ባለቤት ገለጻ አንፃር ለመፈከር የሚያስችሉ ጥያቄዎችን በመጠየቅ ለጥናቱ በቂና ትክክለኛ የሆኑ መረጃዎችን ለመሰብሰብ ስለሚያስችል ተመርጧል።እንዲሁም ከክዋኔው ውጭ ማህበረሰቡ ለምን፣ለማን፣ለማህበረሰቡስ ያለው ማህበራዊና ስነልቦናዊ ፋይዳ ምንድነው? የሚሉትን ጉዳዮች ለመረዳት አመቺ ስለሆነ ተመርጧል።

በቃለ መጠይቅ ወቅት በማህበረሰቡ የባህላዊ አስተዳደር ስርዓተ ክዋኔ ወቅት የሚተገብራቸውን ልማዳዊ ድርጊቶች፣ቁሳቁሶች፣ምግብና መጠጦች እንዲሁም አልባሳትናቃላዊ ግጥሞች ወዘተ. የክዋኔው አካል የሆኑ ፎክሎራዊ ገጽታያላቸውን ጉዳዮች ከማህበረሰቡ ማህበራዊ ስነልቦናዊ አተያይና አረዳድ አንፃር በጥልቀት ለመረዳት አመቺ ስለሆነና ከመረጃ አቀባዮች የሚገኘው መረጃ የበለጠ ግልጽ ለማድረግ ስለሚረዳ በዚህ ጥናት በሁለተኛ ደረጃ ለመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያነት ተመርጧል።

በቃለ መጠይቅ ለመረጃ አቀባይነት የተመረጡት ግለሰቦች በፆታ ወንድናሴት፣በእድሜ ደግሞ ከ45 አመት በላይ የሆኑ ስለማህበረሰቡ ባህል የተሻለ (ስለ ሀገረሰባዊ አስተዳደር መሪ መረጣ) ግንዛቤ ያላቸው ተብሎ ከማህበረሰቡ በተደረገ ጥቆማ መሰረት የአካባቢው ተወላጅ የሆኑ ሃያ ሰዎች (20) ናቸው።ሃያ ሰዎች ለቃለ መጠይቅ የተመረጡበት ዋና ምክንያትም በትግራይ ክልል ተከስቶ በነበረዉ ጦርነት ሳቢያ ጥናትለሚካሄድበት ርእስ በቂ መረጃ መስጠት የሚችሉ የእድሜ ባለጸጋ አባቶች እና እናቶች ተፈናቅለዉ ከቀያቸዉ ስለተሰደዱ በቀላሉ ለማግኘት አዳጋች በመሆኑ ነዉ።የዘዘጋጁት ጥያቄዎች ከሚፈለገው መረጃ አንፃር ነፃና ከፊል- ነፃ የሚሉትን የቃለ መጠይቅ አይነቶችን አጥኚው ተጠቅሟል።በነፃ የቃለመጠይቅ አይነት አጥኚው ሰፋ ያለ ሀሳብ ሊነሳባቸው የሚችሉ ጥያቄዎችን ቀድሞ በማዘጋጀት መረጃ ሰጪዎች በነፃነት እንዲሳተፉ በመፍቀድ መረጃዎች ተሰበስቧል።

በከፊል ነፃ የቃለመጠይቅ አይነት ደግሞ መረጃ አቀባዮች ከቀረበላቸው ጥያቄ ተነስተው ከሚሰጡት ምላሽ በመነሳት አጥኚው ለምን፣እንዴት፣ለማን፣የት፣መቼ የሚሉትን ጥያቄዎች በማንሳት በመሀል ጣልቃ በመግባት መረጃዎች ሰብስቧል።በመሆኑም በምልከታ ወቅት የሚከወኑ ስርዓቶችን ከሚባለው ቃላዊ፣ከሚከወንበት ቁሳዊናመንፈሳዊ ትዕምርቶች በመነሳት ለምን? የሚለውን ጥያቄ በማስገባት እና እንዲሁም በከፊል ነጻ ቃለመጠይቅ ወቅት ከርዕሰ ጉዳዩ እንዳያፈነግጡ ከሰፊው መነሻቸው ወደ ሚፈለገው ጉዳይ ጎትቶ በማምጣት መረጃዎች ተሰብስቧል።

## 3.3 ተተኳሪ ቡድን ውይይት

የቡድን ውይይት በሶስተኛ ደረጃ ለዚህ ጥናት ለመረጃ መሰብሰቢያነት የተመረጠ ዘዴ ነው።የተመረጠበት ምክንያት በምልከታና በቃለመጠይቅ ያልተመለሱ ጥያቄዎችን ለመመለስና የጎደለ መረጃ ካለ የመረጃ ክፍተትን ለመሙላት በማሰብ ነው።መረጃ ሰጪዎች ብዙውን ጊዜ በተናጠል ሙሉ የሆነ እውቀት አይኖራቸውም።ይሄውም የመርሳት፣የመሳት፣በጉዳዩ ላይ በቂ ልምድና እውቀትያለ መኖር ሊያጋጥም ይችላል።ይህም ዘዴ የተመረጠው በቡድ ንውይይት ወቅት ያንዱን ክፍተት ሌላኛው እየሞላ ስህተቶች እየታረሙ የተረሱና ከቁጥጥር ውጭ የሆኑት መረጃዎች ከግምት ውስጥ እየገቡ ትክክለኛ መረጃዎች ለማስገኘት ሚናው የጎላ ስለሆነ ነው።ስለሆነም በማህበረሰቡ የሀገረሰባዊ አስተዳደር ሰርአተ ክዋኔ ላይ በምልከታና በቃለመጠይቅ የተሰበሰቡመረጃዎች አጠራጣሪና እርግጠኛነት የጎደላቸው መረጃዎች ካሉ ለባህሉ የበለጠ ግንዛቤ ያላቸውን በእድሜ ከ45 በላይ ይሆናቸዋል ተብሎ የሚታሰቡትን 5-10 ያህል ሰዎችን በመምረጥ የዖታ ስብጥርን ባማከለ መልኩ ቡድን በማዘጋጀት ተካሂዷል።

## 3.4 ሰነድ ፍተሻ

በአራተኛ ደረጃ ለዚህ ጥናት ለመረጃ መሰብሰቢያነት የተመረጠ ካልዓይ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ ነው።ርዕሰ ጉዳዩን የተመለከቱ ንድፈ ሀሳቦችና ፅንሰ ሀሳቦችን ከተለያዩ መፃህፍት፣መጣጥፎች፣ከቤተ መፃህፍትና ኢንተርኔት እንዲሁም ከጥናቱ ጋር ተያያዥነት ያላቸውን ጥናቶች በካልዓይ የሰነድ ፍተሻ የመረጃ ምንጭነት አጥኚው ተጠቀሟል።በመሆኑም በወረዳዉ ባህልናቱሪዝም ቢሮ ባለሙያዎች የተሰበሰቡ ስለ

ብሔረሰቡ ማህበረ ባህላዊ ዳራና ስርዓት ክዋኔን የሚገልጹ ጽሁፎችንና ቪዲዮ ቀረፃዎችን አጥኚው ተጠቀሟል።

### 3.5 የናሙና አመራረጥ ዘዴ

ይህ ጥናት ኢላማ ተኮር (Purposive sampling) የናሙና አመራረጥ ዘዴ የተከተለ ነው።ኢላማ ተኮር የተመረጠበት ምክንያት በጥናቱ ወሰን እንደተገለጸዉ በተጠቀሱ ቦታዎች በቂ

መረጃ ሰጪዎችን ማግኘት ስለሚቻል ነው።አንድ የመስክ ተመራማሪ በቂመ ረጃዎችን

በምን ሁኔታ እና ከማን ማግኘት እንደሚችል አላማ ይዞ መውጣት እንዳለበት፣(Purposive sampling) መጠቀም ደግሞ አላማውን ከግብ ለማድረስ እንደሚረዳዉ (Kumar, 1991: 62) ይገልጻል።በዚህ መሠረትም የኢሮብ ብሔረሰብ በብዛት የሚገኙባቸው እና ለደህንነት አመቺ የሆኑትን ቀበሌዎች የተመረጡ ሲሆን፤የመረጃ ሰጪዎችን ናሙና አመራረጥ በተመለከተ እንዲሁ መረጃ በመስጠት የጥናቱን አላማ ለማሳካት ይረዳሉ ተብሎ የታመነባቸዉ20 ሰዎች በመምረጥ በጥናቱ የታሰተፉ ይሆናል።በዚህ ጥናት ጾታ በተመለከተ ከሁለቱም ጾታዎች መረጃ ተሰበሰቧል።

### 3.6 የመረጃ አደረጃጀትና መተንተኛ ስልት

#### 3.6.1 የመረጃ አደረጃጀት ስልት

ከመስክ በምልከታ፣በቃለመጠይቅ፣በቡድን ውይይት እና በሰነድ ፍተሻ የተሰበሰቡ መረጃዎች አውዱን በጠበቀ መልኩ ከማህበረሰቡ እሳቤና አረዳድ አንፃር ወደ ጽሁፍ /ትራንስክራይፕ/ ተደረጓ።በመቀጠልም ለትንታኔ ያመች ዘንድ መረጃዎች በፈርጅ በፈርጃቸው ተደራጅቷል።አካባቢያዊና አካዳሚያዊ የዘውግ ምደባ ስልቶችን በቅንጅት በመጠቀም ከማህበረሰቡእሳቤና አረዳድ አንጻር መረጃዎች ይዘትን መነሻ በማድረግ በዘውግ በዘውጋቸው ተመደቧል።ምደባውም የተካሄደው መረጃዎች ካላቸው ተዛምዶና ቅርበት አንፃር በዘር በዘራቸው ነው።ይሄውም በአብይና በንዑስ ክፍሎች ተመድዷል።በመቀጠልም ቁልፍ መረጃዎች ማለትም ይበልጥ ከጥናቱ ርዕሰ ጉዳይ ጋር አብረው ሊሄዱ የሚችሉ መረጃዎች

ለትንታኔ ተመረጧል።ማለትም የብሂረሰቡን የሀገረሰባዊ አስተዳደር ክዋኔን ግልጽ በሆነ መልኩ ሊገልጹ የሚችሉትን ለትንታኔ ተመርጠው ተፈክሯል።

## ምዕራፍ አራት

# የኢሮብ ብሔረሰብ አጠቃላይ ዳራዎች እና በኢሮብ ብሔረሰብ የሀገረሰባዊ አስተዳደር መሪ (ኦና) መረጣ ሰርአተ-ክዋኔ ትንተና

## 4.1.የኢሮብ ብሔረሰብ አጠቃላይ ዳራዎች

ይህ ምዕራፍ ጥናቱ የሚካሄድበትን የኢሮብብሔረሰብ አጠቃላይ ገፅታየሚያስተዋውቅ እና የሀገረሰባዊ አስተዳደር መሪ (ኦና) መረጣ ሰርአተ-ክዋኔን የሚተነተንበት ነው። በስሩም የኢሮብብሔረሰብ አመጣጥ ታሪክ፣ ቋንቋ እና እምነት፣ መልክዓምድር፣ የአየር ንብረት እና ስነ ህዝብ እና ኢኮኖሚ በተመለከተ በአጭሩ ገለጻ ቀርቦበታል። የብሔረሰቡ ዳራዊ ማስረጃዎችን የተካተቱትም ከመስክ የሚሰበሰበዉን መረጃ ለመተንተን አጋዥ ስለሚሆን ነው። “አንድን ሰርአተክዋኔን ለመረዳት የባለቤቱንባህል ማወቅ ይገባል” በማለት (Fischer, 1963, 247) እንደሚገልጸዉ‚እነዚህ ማስረጃዎችም በሚቀጥለው ምዕራፍ ለተደረገው ትንተና የራሳቸው ድርሻ አላቸው የሚል እምነትም ስላለ ነው።

### 4.1.1 የኢሮብ ብሔረሰብ አመጣጥ ታሪክ

ሳሆ ቋንቋ ተናጋሪ ህዝቦች በሁለቱም ሀገር ማለትም በኢትዩጵያና ኤርትራ ዉስጥ የሚገኙ ሆኖ በአምስት ቡድን ይከፈላሉ:: እነሱም :-ዓሳቡርታ ፣ሚኒፍረ፣ ዳብሪ ሜላ፣ሓዞ እና ኢሮብ ናቸዉ። ከነዚህ አምስቱ ቡድኖች የኢሮብ ብሔረሰብ ከሚኖርበት ቦታ፣ካለዉ ባህል፣ ከሚከተለው ሃይማኖትና ኢኮኖሚ እንቅስቃሴ አንጻር ይለያል። ስለዚህ የኢሮብ ብሔረሰብ ታሪካዊ አመጣጥ እና ስም በተመለከተ የተለያየ እሳቤ ያለ ሲሆን አንዳንዶች ኢሮብ የሚለው ቃል አዉሮፓ ከሚለው ቃል በማመሳሰልና ከእስክንድር የመንደር ልጅ ዘር ጋር በማገናኘት ህዝቡ ከአዉሮፓ አሁን ወዳለበት አከባቢ ከክርስትና እምነት መምጣት ጋር ተያይዞ የመጣ ህዝብ እንደሆነ ሲናገሩ በሌላ በኩል ደግሞ የብሂሩ የእድሜ ባለጸጋ ሽማግሌዎችና ልቃዉንት ኢሮብ የሚለው የብሔሩና የአከባቢው ስለ መጠሪያ ስም የሆኖ ኣውሮፓ ከሚለው ቃል ሳይሆን ኦሮባ ከሚለዉ ቃል የተገኘ ትርጓሜዉም ወደ ቤት ይግቡ ማለት ነው በማለት የቃሉና ስያሜው ትርጉም ያስረዳሉ ። (ብርሃነ ጽጋብ2010፣4-5)

ኢሮብ በአሁኗ ትግራይ ክልል ሰሜናዊ ምስራቅ የምትገኝ ወረዳ ናት ። የኢሮብ ማዕከልና ለረጅም ዓመታት ዋና ከተማ የነበረችው 'ዓሊቴና' የሚትባል ቦታ ስትሆን ከክልሉ ዋና ከተማ መቐለ 155 ኪሜ የምስራቃዊ ዞን ዋና ከተማ ከሆነችው ዓዲግራት ደግሞ 45 ኪ/ሜ ርቀት ላይ ትገኛለች ። ኢሮብ ላለፉት 28 ዓመታት "በልዩ ወረዳነት" ስትመደብ የአሁኑዋና ከተማ ደግሞ "ዳውሓን" ትባላለች ። ዳውሓን'ም ለዓሊቴና ቅርብ ስለሆነች ከዓዲግራት ተመሳሳይ ርቀት ላይ ትገኛለች ። ዋና ከተማዋ ዳውሓን እጅግ አነስተኛ በሆነ የመሬት ስፋት ላይ ያረፈች ከተማ ናት ።

ኢሮብ በምዕራብ አቅጣጫ ሙሉ በሙሉ በትግርኛ ተናጋሪ ሕዝቦች ጋር የምትዋሰን ሲሆን፣ ይህንን ምዕራባዊ መስመር ይዘን ወደ ሰሜን አቅጣጫ ስንጓዝ ኢሮብ በጉሎማክዳ ወረዳ ስትዋሰን፣ ቀሪው ደግሞ በኤርትራው የአካለ-ጉዛይ ትግርኛ ተናጋሪ አጎራባች ሕዝብ ትዋሰናለች። ቀጥሎ ያለው ሰሜናዊ ጫፍ ደግም ከአምባ ሶይራና ማኮ ከሚባሉ የኤርትራ የመሬት ይዞታ እና ሴሚናዊ የኢሮብ ጫፍ የመሬት ይዞታ መኻል ሰንጥቆ ወደ ዒንደሊ በሚወርደው ወንዝ ትዋሰናለች። አሁንም ይህን ወንዝ ሳንለቅ ተከትለን ከሰሜን ጫፍ የምስራቁን አቅጣጫ ይዘን ወደ ደቡባዊ ጫፍ እስክንደርስ ደግሞ በኤርትራዊያን የሳሆ ቋንቋ ተናጋሪ ህዝብ ጋር ትዋሰናለች። ዙረን ወደ ደቡባዊው ጫፍ ስንመለስ ደግሞ በዓፋር ክልልና ከሳዕሲዕ-ፃዕዳእምባ ወረዳ ጋር ትዋሰናለች።

የኢሮብ ምስራቃዊ ወሰን ራንዳ-ኮማ እና ራጋይሊ ድረስ ስለሚዘልቅ እስከ ቀይ ባሕር የሚተርፈው የየብስ ርቀት ሩቅ አይደለም።

በሌላ አነጋገር ከየትኛውም የትግራይ መሬት እንደ ኢሮብ ለቀይ ባሕር የቀረበ ቦታ የለም። የኢሮብ ሕዝብ ከነዚህ አጎራባች ሕዝቦች በሰላም በመከባበርና በፍጹም መግባባት የኖረና የሚኖር ሕዝብ ነው። ማሕበረ-ኢኮኖሚያዊ ትስስሩም የተሳሰረና የተጋመደ ነው። "ኢሮብ' ሲባል የማሕበረሰቡና የወረዳው የጋራ ስያሜ የሚወክል ሲሆን፣ ወረዳ = ኢሮብ ፣ ማሕበረሰብ = ኢሮብ ፣ በመባል ይታወቃል። በ2007ዓ/ም የፌዴራል ስታቲስቲክስ ኮሚሽን ባወጣው አሃዝ መሰረት የኢሮብወረዳ አጠቃላይ የህዝብ ብዛት 25,862.4 በሌሎች የተከበበ 90% የኢሮብ ብሔረሰብ በነባሩ ወረዳ አስተዳደርየሚኖሩ አዳጋዴአሬ፣ቡክናይቱ-አሬ፣ እና ሓሳባላ የሚባሉት የሶስቱ ወንድማማቾች ዘሮች ናቸው ተብሎ ይታሰባል። እነዚህ ሦስቱ የኢሮብ ወንድማማቾች ሱመ የሚባል የአንድ ሰው ዘር ነን ብለውም ያምናሉ።የኢሮብ ሕዝብ የራሱ ወግ፣ ባህልና እሴቶች እንዲሁም የራሱ የሆነየፓለቲካ-እሳቤና የግንባታ ታሪክ ያለው ሕዝብ

ነው። አዋሳኝ ትግርኛ ተናጋሪ ሕዝቦች አከባቢውን "ዓዲ-ኢሮብ" በማለት ሲጠሩት ነዋሪውን ደግሞ "ሕዝቢ-ኢሮብ" ይሉታል። ሳሆ ተናጋሪዎች ሕዝቡን 'ኢሮብ' መሬቱን ደግሞ 'ኢሮብ-ዲክ/ኢሮብ-ባዶ' በማለት ሲጠሩት፣ የሁለትዮሽ ማሕበራዊ ትስስሩን "ኢሮብከ-ሓዶ"፣ በሚል ሲገልጹት ኢሮቦችም በተመሳሳይ ሓዶከ-ኢሮብ በማለት የተለየ ቅርበትና ሚዛን ይሰጡታል።

የኢሮብ ሕዝብ አስመልክቶ ብዙዎችን ሲያወዛግብ የሚታየው ጉዳይ ቢኖር የኢሮብ ሕዝብ ልክ እንደ ዓፋርና ኩናማ በኤርትራና በኢትዮጲያ ውስጥ ይካለላል ወይም ይኖራል የሚል ሲሆን፣ መልሱ ግን አጭርና ግልፅ ሆኖ የኢሮብ ሕዝብ የሚገኘው ኢትዮጲያ ትግራይ ውስጥ ብቻ ነው። ይህ ብቻ ሳይሆን የኢሮብ ሕዝብ በመዋዕሉ ኤርትራ ውስጥ የተካለለበት ወይም የተዳደረበት አንዳች ወቅት አልነበረም፣ ኖሮም አያውቅም። እንዲያውም እንደ እውነቱ ከሆነ ዘመናዊ የአከላለል ስርዓት ተጀምሮ ተግባራዊ ከመሆኑ በፊት በራሱ አካባቢና የአስተዳደር ስርዓት፣ ማንነቱን ጠብቆ የኖረ ሕዝብ ነው። የራሱ ሕግጋት በማርቀቅ ልክ እንደ ዘመኑ ቃለ ጉባኤ ያኸ በመሰየምና በየርዕሱ የሚይዙ ሰዎች በመሰየም በሕግ አግባብ ሲተዳደር ነበር። (ለምሳሌ፤ ቃለጉባኤ ለመያዝ የተለየ የማስታወስ ተሰጥዎ ያላቸው ሶሰት ሰዎች የሚመረጡ ሲሆን የውሳኔ አሰጣጥ ላይ ብዥታ ሲፈጠር እነዚህ ሰዎች ይጠሩ ነበር ይባላል) ይህ ብቻ ሳይሆን በአግባቡ ስላልተሰነደ ነው እንጂ ሌላውን የአከባቢ ሕዝቦችን ከዘመናዊ ሕግጋት ጋር ያስተዋወቀ ሕዝብ ነው።https://advocacy.irobpeople.org/

### 4.1.2 የብሔረሰቡ መልክዓ ምድራዊ አቀማመጥና አየር ንብረት

የኢሮብብሔረሰብ በትግራይ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስቲ ምስራቃዊ ዞን በሰሜን ምስራቅ በኩል ከአዲ ግራት ከተማ 47ኪ ሜትር ርቀት ላይ በምትገኝ ወረዳ ኢሮብ ተብላ በምትታወቅ ወረዳ የሚገኝ ብሔር ሆኖ ሰፍሮ የሚገኝበት የመሬት አቀማመጥ ሜዳማ 1%፣ 85% ተራራማና 14% ደግሞ ሸለቋማ ሲሆን ከባህር ወለል በላይ 1200-3000 ሜትር ከፍታ የሚደርስ መልክዓ ምድራዊ ገጽታ አለው። የአየር ንብረቱ ደግሞ ደጋ፣ ወይና ደጋ እና ቆላማ ነው። አመታዊ የዝናብ መጠኑ በአማካይ 140-400 ሚ.ሜ ሲሆን አመታዊ የሙቀት መጠኑ ደግሞ በአማካይ ከ15-30 ዲግሪ ሴንትግሬድ ይደርሳል። Irob Mountain Livelihood Zone February 2007-4

### 4.1.3 የብሔረሰቡ እምነትና አምልኮ

የኢሮብ ሕዝብ ሙሉ በሙሉ በሚባል ደረጃ የክርስትና ሃይማኖት ተከታይ ሲሆን እጅግ አነስተኛ መጠን ያላቸው የእስልምና ተከታይ ነዋሪዎችም ይገኛሉ። ከዚሁ ጋር ተያይዞ አብዛኞቹ ሰዎች የኢሮብ ሕዝብ የካቶሊክ ሃይማኖት ተከታይ ብቻ እንደሆነ ይገምታሉ። ግምቱ ግን የግንዛቤ ክፍተት ከመሆኑ ውጭ መሬት ላይ ያለ ሃቅ አይወክልም። ይልቁንም ከኢሮብ ሕዝብ የካቶሊክ ተከታዩ 1/3ኛ ገደማ ብቻ ሲሆን አብላጫው የኦርቶዶክስ እምነት ተከታይ ነው። የኦርቶዶክስ ሃይማኖት በኣከባቢዉ ከሁሉም የቀደመ ረጅም ዕድሜ አለው። የኢሮብ ህዝብ የደቂቀ ኢስጢፋኖስ ተከታዮችን በመቀበልና በማስተናድም ይታወቃል። ሁለቱንም፣ ማለት የቆየው የኦርቶዶክስ-ተዋህዶ እምነት ተከታዮችንና ደቂቀ ኢስጢፋኖስችን ጎን ለጎን አስተናግዷል። ከዚህም ጋር ተያይዞ ጥንታዊ የጉንዳጉንደ ገዳም የሚገኘው በኢሮብ ወረዳ ሲሆን፤ ለግዞተኞች የደቂቀ ኢስጢፋኖስ መነኮሳት መጠግያ እንዲሆናቸው የኢሮብ ህዝብን በማስተባበር ጉንዳጉንዴን ያስገነባው ቡሩ ሱባጋዲስ የሚባሉ የሓሳባላ-ኢሮብ ተወላጅ ናቸው። ገዳሟ የተገነባችው ዓሲምባ ተራራ ግርጌ ስር ካለው ሰዋራ ቦታ ሲሆን፤ ሽሽት ላይ ለነበሩ መነኮሳት እጅግ አመቺ ሆናላቸዋለች። የደጃች ሱባጋዲስ አስከሬንም በኑዛዜያቸው መሠረት ወደ ትውልድ ቦታቸው እንዲመለስ ሆኖ በዚችው ገዳም ተቀብሯል። አሁንም የደጃች ሱባጋዲስ አስከሬንና የሁለት ልጆቻቸው (የደጃች ወልደሚካኤልና የደጃች ሓጎስ) ሬሳዎች የያዙ ሳጥኖች በገዳሙ ቅጥር ውስጥ ተቀምጠው ይገኛሉ።በተመሳሳይ በሰሜኑ ያገራችን ክፍል የካቶሊክ እምነትን ተቀብሎ በማስተናገድ አሁንም የኢሮብ ሕዝብ ቀዳሚ ነው። ቀጥሎም መነሻውን ዓሊቴና በማድረግ ወደ ሰሜን አቅጣጫ ተስፋፍቶ ኤርትራን ቀጥሎም ሌሎች የኢትዮጵያ ክፍሎችን እንደአዳረሰ ይታወቃል።ብርሃነ ጽጋብ (2010 -4)

### 4.1.4 የብሔረሰቡ ቋንቋ

በኢሮብ ብሔረሰብ ታሪካዊ አመጣጥ ላይ ለመጥቀስ እንደተሞከረዉ ሳሆ ቋንቋ ተናጋሪ ህዝቦች በሁለቱም ሀገር ማለትም በኢትዩድያና ኤርትራ ዉስጥ የሚገኙ ሆኖ በአምስት ቡድን ይከፈላሉ:: እነሱም :-ዓሳቡርታ ፣ሚኒፍረ፣ ዳብሪ ሜላ፣ሓዞ እና ኢሮብ ናቸዉ። ከነዚህ አምስቱ ቡድኖች የኢሮብ ብሔረሰብ ከሚኖርበት ቦታ፣ካለዉ ባህል፣ ከሚከተለዉ ሃይማኖትና ኢኮኖሚ እንቅስቃሴ አንጻር የሚለይ ሆኖ ምንም እንካን የምናገረዉ ቋንቋው ስም ሳሆ ቢሆንም ቋንቋዉ በግእዝ አቦጊዳ(Alphabet of the Language) የሚጻፍናየአነጋገር ዘዬው የሚለይ

ነው። ከኢሮብ ዉጪ ሳሆ ቋንቋ ተናጋሪዎች በግእዝ ሳይሆን በላቲንኛ ነዉ የሚጽፉት።(ብርሃነ ጽጋብ2010 -9)

### 4.1.5 የብሔረሰቡ ኢኮኖሚያዊ ሁኔታ

የህዝቡ ዋነኛ መተዳደሪያ እንስሳ እርባታ እና ግብርና ሲሆን ለተለያዩ ተግባራት የሚውሉ የእደጥበብ ምርቶችንም ያመርታሉ። ከእህል ሰብል በቆሎ፣ ማሽላ፣ ጤፍ፣ ገብስ እና ስንዴ፣ ከጥራጥሬ ባቄላ እና አተር ከፍራፍሬ ብርቱካን እና በተለይ ማርና የማር ዉጤት፣ እንዲሁም ወተትና የወተት ውጤቶች ዋነኛው የገቢ ምንጫቸው ናቸው::Irob Mountain Livelihood Zone February 2007-4

## 4.2 ኦና ሰርአት

ኦና ስርዓት ማለት የአከባቢዉ ከፍተኛ መሪን የመምረጥ እና በሰርአቱ የመመራት ሂደት ሆኖ የኢሮብ ህዝብ በጋራ በፈጠረው ሕግና ደንብ የተደራጀ ነበር:: የኢሮብ ብሔረሰብ ባህላዊ የአስተዳደር ሰርአት የሆነው የኦና ሥርዓት ከኢሮብ ብሔር ሁለንተናዊ ሕይወትና ዕድገት ጋር በእጅጉ ተያያዥነት ያለው ሲሆን ሥርዓቱ ከቀላል እስከ ውስብስብ ወደሆነ ማህበራዊ ጉዳዮችን የሚዳስስ ባህላዊ የአስተዳደር ሥርዓት ነው። ይህ የኦና ሥርዓት የኢሮብ ብሔረሰብ ለረጅም ዘመናት ሲተገብረው ከመቆየቱም በላይ በሂደትም እያዳበረውና እያሳደገው የኖረበት ራሱን በራሱ የሚተዳደርበት የጋራ መተዳደሪያ ህጉም ነዉ። ይህንን የኦና ሥርዓት የኢሮብ ብሔር አባላት የማንነት መገለጫ የሆኑ አንኳር ባህላዊ ገጽታዎች፣ ታሪክና እምነት እንዲሁም ሀገር በቀል የሆነ እውቀትን አካቶ የያዘ ጥንታዊ የዴሞክራሲያዊ አስተዳደር ሥርዓቱም ጭምር ነው።

የኢሮብ ብሔረሰብ እስከ ዘመነ መንግስት ንጉሰ ነገስት ሃጸይ ሃይለስላሴ ድረስ ራሱን በራሱ የሚያስተዳድርበት " ኦና" ተብሎ የሚታወቅ ባህላዊ የአስተዳደር ሰርአት እንደነበረዉና ኦና ማለትም ህዝቡ በራሱ ነጻ ፍቃድ እና ተሳትፎ እንዲመራዉ ለሚመርጠዉ ባለስልጣን የሚሰጠዉ የሹመት መጠርያ ስሆን ትርጉሙም ዋና ማለት ነዉ። ህዝቡ እንዲመራበት ተወያይቶ ያጸደቀዉ ሰርአት መጠርያ ደግሞ ኦኒ ሰርአት (የኦና ሰርአት) ይባላል። ይህ ባህላዊ ሰርአት እንደ መመሪያ ይገለገልበት የነበረዉ ህግ ያልተጻፈ ሆኖበጊዜዉ የነበረዉን አጠቃላይ የማህበረሰቡና የተፈጥሮ ሁኔታ ታሳቢ በማድረግ ያልተጻፈ ቢሆንም ህዝቡ ተግባራዊ ያደርገው የነበረ ሰርአት ነዉ።(ዝግታ ሓድጉ2008 :2)

ከመረጃ አቀባዩች የተገኘዉ መረጃ መሰረት የኦና ሰርአት ህጎች አወጣጥ በአጠቃላይ ሲታይ ውጫዊ እና ዉስጣዊ ተብሎ በሁለት ይከፈላሉ።

### 4.2.1 የኦና ሰርአት ህጎች ውጫዊ ገጽታ

ኢሮብ ብሔረሰብ ከአጎራባች ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች ጋር ማነኛውም ግጭት ከመፈጠሩ በፊት በሰላም እንዴት መኖር እዳለባቸውና የሰው ልጅ ተፈጥሮአዊ ባህሪየሆነው ግጭት ከተፈጠረ ደግሞ የተፈጠረዉን ግጭት እንዴት መፈታት እንዳለበት በተለያዩ ዘመን የነበሩ የብሔረሶችና ህዝቦች ሊቃዉንት በዓጋመ፣ ስሩኩሶና ሓዞ እንዲሁም በማንጋላሎና ዳዕሮሰንገደ በሚባሉ አከባቢዎች በመገናኘት ረዘም ያለ ጊዜ በመውሰድና በጥንቃቄ የጋራ መተዳደሪያ ባህላዊ ህጎች በማውጣት ተግባር ላይ ያውሉት እንደነበር ከመረጃ አቀባዩቹ አንዱ የሆኑት መ/ር በርሀ ዝግታበዓዲ ግራት ከተማ 20/07/2016 ዓ/ም መስክሯል።

ይህንን የጋራ ህጎች ለማውጣት እንደ መነሻ ብዙ ጉዳዮች የነበሩ ቢሆኑም በዋናነት ግን የኢሮብ ብሔረሰብ አጠቃላይ ኢኮኖሚውበአብዛኛው በእንስሳ እርባታ ላይ የተመሰረተ በመሆኑ የዝናብና ሳር እጥረት ስያጋጥም እንስሳ ይዞ ከቦታ ወደ ሌላ ቦታ መንቀሳቀስና መሰደድ የተለመደ ስለነበርና በዚህም ምክንያት የከብት መዘራረፍ ወይም መሰራረቅን ተከትሎ መጣላትና መገዳደል ወንጀል እየገነነ በመምጣቱና ጉዳዩ ስር ከመስደዱ በፊት ለማስቆምና ለመቆጣጠር ሲባል ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ጉዳዮችን ማእከል በማድረግ የጋራ ህግ ማውጣታቸውን መረጃ አቀባይ መ/ር በርሀ ዝግታ ተናሯል።

☐ ዘመኑ ከፍቶ የዝናብና ሳር እጥረት ሲያጋጥም ከአንዱ ቦታ ወደ ሌላ ቦታ ለሚሰደድ ሰው መደረግ ያለበት እንክብካቤ።

☐ በሆነ አጋጣሚ የእንስሳ መዝመት በአንዱ ወገን ከተደረገ በምን አግባብ እልባት ማግኘት እንዳለበት።

☐ በአንድ አከባቢ ወንጀል ፈጽሞ ወደ ሌላ አከባቢ ተሰዶ ጥገኝነት ለሚጠይቅ አካል ምን አይነት አያያዝ ሊደረግለት እንደሚገባ።

☐ የወሰን ይገባኛል ጥያቄ ከአንዱ ወገን ሲነሳ ምን መደረግ እንዳለበት።

☐ በአንዱ ወገን የሴት ጠለፋ ከተደረገ ጉዳዩን እንዴት መፍታት እንደሚቻል።

☐ በተለያዩ ወገን መካከል የግድያ ወንጀል ከተፈጸመ እንዴት እልባት ማግኘት እንዳለበት የሚሉ ነጥቦች መሰረት በማድረግ ህግ ያወጡ ነበር።

## 4.2.2 የኦና ሰርአት ህጎች ውስጣዊ ገጽታ

ይህኛዉ የኦና ሰርአት ህጎች ዉስጣዊ ገጽታ በዋናነት የኢሮብ ብሔረሰብ ዉስጣዊ ጉዳዩቻቸዉን እንዴት ማስተዳደር እንዳለባቸዉ የሚያሳዩ ህጎችን ያካተተ ስሆን የብሔሩ ሶስት ጎሳዎች ማለትም ሓሰበላ፣እንዳልገዳ እና ቡክናይታ የሚባሉ ጎሳዎች ሓንታካር፣ ቦካለ ማኮ እና ሞጎደት ዳጋ በሚባሉ የኢሮብ ቦታዎች በመገናኘት ጊዜ ወሰደዉና የህዝባቸዉና አከባቢያቸዉ ነባራዊ ሁኔታዎችን ግምት ዉስጥ በማስገባት የኢሮብ ብሔረሰብ ሊተዳደሩበት ያወጡት ውስ-ዊ ህጎችን የሚያሳይ ሆኖ ይህ ህግ ከሰዉ፣ ተፈጥሮና እንስሳ ጀምሮ የማይዳስሰዉ ጉዳይ የለም ማለት ይቻላል ይላሉ መረጃ አቀባዩቹ። ጠቅለል ባለ መልኩ ስታይ የኦና ሰርአት ከዚህ በታች የተዘረዘሩት ጉዳዩችን ያጠቃልላል:-

☐ ሀገረሰባዊ የአስተዳደር መሪ(የኦና) መረጣ ጉዳይ

☐ የግድያ ወንጀል አፈታት

☐ የአካል ጉዳት ወንጀል አፈታት

☐ የሴት ጠለፋና መደፈር ጉዳይ አፈታት

☐ ጋብቻን የሚመለከቱ ጉዳዩች

☐ ፍቺን የሚመለከቱ ጉዳዩች

☐ የእንስሳ አካል ጉዳት ወንጀል አፈታት

## 4.3 የኦና ሰርአት መሰረታዊ ባህርያት

የኦና ሰርአት ሶስት የህግ አካላት የነበሩት ስሆን አንደኛዉ ህግ አዉጭዎች የሚባሉት ከሁሉም ጎሳዎች ባላቸዉ እዉቀት፣ ልምድና ስነ ምግባር የተመሰከረላቸዉ ሽማግሌዎች ሁለተኛዉ ህግተርጓሚ የሚባሉት ሆነዉየሚመረጡትም በህዝቡ ተሳትፎ የጸደቀዉ ህግ በአተገባበሩ ላይ ስህተት እንዳይፈጠርና የተኛዉ ህግ መቼ እና ለምን አላማ እንደጸደቀ የሚከታተሉ ናቸዉ። ሶስተኛዉ ደግሞ ህግ ፈጻሚዎች የሚባሉ ሆኖ የወጣዉን ህግ ተግባራዊ የሚያደርጉ ናቸዉ።

የኦና ሰርአት እንደ ዘመናዊ የኢትዩጵያ ህገ መንግስት ሶስት የህግ አካላት የነበሩት ከመሆኑም በተጨማሪ ከዚህ በታች ያሉት መሰረታዊ ባህርያት ያካተተ እንደነበር መረጃ አቀባዩች የሆኑት መ/ር በርሀ ዝግታ እና አቡነ ተስፋስላሴ መድህን ይናገራሉ።

☐ ፍጹም ህዝባዊ ተሳትፎን ያማከለ መኖሩ።

☐ ማነኛዉም የኦና ሰርአት ህግ አካል የሆነዉን በተግባር ይዉል የነበረዉ፤ ህግ ማስተካከያ ወይም ማሻሻል የሚያስፈልገዉ ከሆነ በኦና ሰርአት አግባብ ጊዜ ተሰጥቶዉ በችኮላ ሳይሆን በማስተዋልና በትእግስት ይታይ እንደነበረ።

☐ ህጉ ልኡላዊነት እንደነበረዉ። ማለትም የማእከላዊ መንግስት ጣልቃ ገቢነት እንዳልነበረዉ።

☐ ሰርአቱ በጾታ፣ ሃይማኖት እና ጎሳዎች መካከል መለያየት ወይም አድልዎ የማያደር መሆኑ።

☐ በተለየ መልኩ የእንስሳት መብት የተካተተበት ህግ መሆኑ።

☐ የወጣዉ ህግ ዘላቂነት የነበረዉ መሆኑ ማለትም ህጉ ለዘመናት ተግባራዊ እየተደረገ መዝለቁ አሁንም ጭምር ማህበረሰቡ በከፊል ይህንን ሰርአት ተግባራዊ የሚያደርግ መሆኑ።

☐ በዚህ ሰርአት አመካኝነት የተሰጠ ዉሳኔ ሙሉ በሙሉ በህዝቡ ተቀባይነት የነበረዉ መሆኑ። ማለትም ህዝቡ ለይግባኝ ወደ ማእከላዊ መንግስት ወይም ወደ መደበኛ ፍርድ ቤት መሄድ የተለመደ አለመሆኑ።

☐ የኦና ሰርአት ከህግነቱ አልፎ ፍትሃዊና ግልጽ እንደነበረ። ማለትም ህጉ ተፈጻሚ ከመደረጉ በፊት ፍትህ እንዳይጓደል ሲባል ብዙ ማጣሪያና ፍተሻ ተደርጎ ህዝቡ ተሰብስቦ በጉዳዩ ላይ አስተያየት ከሰጠበት ቡኋላ በህዝብ ፊት ዉሳኔ ይሰጥ እንደነበረ።

☐ ከእንስሳት መብት በተጨማሪ የሃብት ተፈጥሮ እንክብካቤ ጉዳይ የህጉ ዋና አካል አድርጎ ማካተቱ የሚሉ ናቸው።

ከላየኛዉ የኦና ሰርአት መሰረታዊ ባህርያት መረዳት እንደሚቻለዉ ብሔረሰቡ ለህግ እና ሰርአት በከፍተኛ ደረጃ ተገዥ የመሆንና ህጉ ለመተግበር የሚያስችል በምክንያታዊነት ላይ የተመሰረተ የጋራ ማህበራዊ ፍልስፍና ባለ ቤት እንደሆነ ነው።በተጨማሪም የዚህ ማህበረሰብ

ወይም ብሔረሰብ ማህበራዊ ፍልስፍና በአካባቢና ወቅታዊ ሁኔት ያልታጠረ፣ ባለፈዉ ዘመን ርእዩተ ዓለም ሳይገደብለአሁኑ ዘመንም በተግባር ሊተገበር የሚችልና የሚገባ ለሁሉ የሚበጅ አስተሳሰብ ያለዉ መሆኑ ለተፈጥሮ እና እንስሳት ከሚሰጠዉ እንክብካቤ በግልጽ መረዳት ይቻላል።

በዚህ ምዕራፍ ከዚህ በመቀጠል በኢሮብ ብሔረሰብ የሀገረሰባዊ አስተዳደር መሪ (ኦና) መረጣ ሰርአተ-ክዋኔ ውስጥ ማህበረሰቡ የሚፈጽሟቸውን ክዋኔዎች ከአዉዳቸው በመሰብሰብ ያላቸውን ትርጉምና ፋይዳ ትንተንተና ቀርቧል።

### 4.3.1 የኦና (መሪ) አመራረጥ ሰርአት ሂደት

በኢሮብ ብሔረሰብ ታሪክ ኦና ሆኖ የሚመረጥ ሰዉ በመካለለኛ የእድሜ ክልልየሚገኝ፣ሃይማኖት፣ጾታ እና ጎሳ ሳይለያይ በእኩልነት የሚመለከትና ማስተዳደር የሚችል፤ በሆነ አጋጣሚ የዉጪ ሃይል አከባቢዉንና ሀገሩን ለመዉረር ስመጣ ህዝቡን አስተባብሮ ለመመከት የሚያስችል ሁለ መናዊ አቅም አለዉ ተብሎ የሚታመንለት፣ ከማእከላዊ መንግስት እና አጎራባች ጎሳዎችና ህዝቦች ጋር ቀጣይነት ያለዉ መልካም ህዝባዊ ተግባቦት በመፍጠር የህዝቦቹ መብት እና ወሰን ልእልና አስከብሮ ማስተዳደር የሚችል እና ህዝቡ በሆነ ምክንያት በየጊዜዉ ለማእከላዊ መንግስት መክፈል የሚገባዉ ግብር መክፈል ስሳነውበህዝቡ ምትክ ግብር መክፈል የሚችል ነው ተብሎ የታመነበት፣ በሽማግሌዎችና ሊቃውንት ተጠንቶ ለህዝብ ቀርቦ ህዝቡ ካመነበት በኋላ ሓዳሎብቲ ማለትም ህዝባዊ ጉባኤ ይጠራል።

ድሮ ጊዜ የኢሮብ ብሔረሰብ የሚሰበሰብበት ዘመናዊ አዳራሽ ስላልነበረዉ ህግ የሚያወጣዉ፣የሚያጸድቀው፣በሰርአቱ መሰረት የሚመራው መሪ የሚመርጠው፣ የተፈጸመ ወንጀል የሚያጣራው እና በጉዳዩ ተወያይቶ ውሳኔ ያስተላልፍ የነበረው በታላቅ ዛፍ ስር ነዉ። ሓዳሎብቲ የሚለው ቃልም ሓዳ እና ኦበ የሚሉ የሁለት ቃል ጥምር ሆኖ ሓዳ ማለት ትልቅ ዛፍ ማለት ሆኖኦበ ደግሞ መውረድ ማለት ነው። ሁለቱም ቃላት አንድ ላይ ሆኖ ወደ ትልቁ ዛፍ መውረድ የሚል ትርጉም ይሰጣሉ። ስለሆነም በኢሮብ ብሔረሰብ ታሪክ ውስጥ ህዝባዊ ጉባኤ የሚከናዉንበት ቦታ ማለትም ሓዳሎብቲ የህዝቡ ህልዉና ጥንካሬ፣ እምነት፣ ፍትህ፣ምንነቱና ልኡላዊነቱ መገለጫ ጉዳዩች የሚከናወኑበት ክቡርና ወሳኝ ቦታ ነው። ምክንያቱም በዚህ ሓዳሎብቲ የሚወሰኑ እና የሚከወኑ ህዝባዊ ጉዳዩችና ህጎች ማንም አያፈርሰዉም። ህዝቡ በራሱ አምኖ የወሰነውን ህግና ውሳኔ በተግባራዊነቱ ማንም እንቅፋት

አይሆንም ነበር። የማህበረሰቡ አካል የሆነ ይቅርና ከአጎራባች ማህበረሰብ የመጣ ግለሰብም ሆነ ቡድን በዚህ ሓዳሎብቲ በህዝብ በጸደቀው ህዝባዊ ህግንና ህዝባዊ መሪን ሊያከብርና ሊገዛ ይገደድ እንደነበረና የሀገረሰባዊ አስተዳደር የበላይ መሪ (የኦና) አመራረጥ ሰርአትም የተካተተበት ሰርአትም መሆኑ መረጃ አቀባይ አባ ጥዑም በርሀ ይመሰክራሉ።በመቐለ 15/08/2016 ዓ/ም።

## 4.3.1 .1 የሀገረሰባዊ አስተዳደር መሪ (የኦና) መረጣ ክዋኔ ቅድመ ዝግጅት

የኦና(መሪ) አመራረጥ ሰርአት ሂደት መሪ በይፋ ማህበረሰቡ በተሰበሰበበት በህዝቡ ድምፅ ከመመረጡ በፊት በመጀመሪያ በተለያዩ መንደሮች የሚኖሩ ሰዎች በየአከባቢዎቻቸው በሚወከሉዋቸው አስተባባሪ ባለፀጋዎች አመካኝነት ተሰብስበው ተወካዮቻቸውን ይመርጣሉ። ከየአከባቢው ተመርጦ የሚላኩ ግለሰቦች የተወካዮች ምክር ቤት ይመሰርታሉ፣ከየአከባቢውተወካዮቻቸውን ከመረጡ በኃላ በየአከባቢው ተወካዮች እንዲወክሉ የሚያስተባበሩ ባለፀጋዎች ተገናኝተውእነዚህ ተወካዮች የሚሰበሰቡበት ጠቅላላ ጉባኤ እና መረጣ ክዋኔ የሚፈፀምበት ቀን የመለየት፣የምግብና መጠጥ አይነቶች ዝግጅት፣ የቁሳቁስና አልባሳት ዝግጅት፣ የስፍራ ዝግጅትና መሰናዶን ማሟላት ናቸው፡፡

## 4.3.1 .2 የሀገረሰባዊ አስተዳደር መሪ (የኦና) መረጣ መከወኛ ጊዜን መለየት

በኢሮብማህበረሰብ የሀገረሰባዊ አስተዳደር መሪ (የኦና) መረጣ ክዋኔ ለመፈፀምየሚመረጡት ጊዜያቶችየአዲስ አመት መግቢያ ወራቶች ማለትም ጥቅምት፣ ሕዳር እና ታህሳስ ወራት ሲሆኑ የተለየ የመከወኛ ዕለታት ደግሞ ቅዳሜ፣እሁድ እና በበአላት ቀን መሆኑን አረጋግጫለሁ፡፡ ይህም በአመት እንደ ሚመረጠው መሪ የጤና፣እርጅና እና ብቃት ሁኔታ መሪ መቀየር ባስፈለገበት ጊዜ ሁሉ ሰርአተ ክዋኔው ይፈፀማል፡፡

የሀገረሰባዊ አስተዳደር መሪ (ኦና) መረጣ ክዋኔ ከተጠቀሱት ወራት እና ዕለታት ጋር ግንኙነት ያለው መሆኑን ለማረጋገጥ ካደረግኩት ቃለ መጠይቅ መረዳት እንደተቻለው የተጠቀሱ ወራት እና ቀናቶች የተለያዩ ሰብሎች ተሰብስቦ የሚገቡበት እና ማህበረሰቡ በአዲስ ተስፋ የሚሞሉበት እና የተሻለ ነገር የሚያቅዱበትና የሚፈፅሙበት ወቅት በመሆኑ ለሚካሄደው ሰርአተ ክዋኔ የተጠቀሱ ወራትና ቀናቶች በተለየ መልኩ ተመራጭ ያደርጋሉ፡፡ ይሁን እንጂ የመረጡት መሪ(ኦና) በጤና፣በእርጅና እና በብቃት ማነስ በመረጠው ህዝብ

ተቀባይነት ከተነፈገና  መሪ መቀየር ካስፈለገ በማንኛው ጊዜ ሰርአተ ክዋኔው ለመፈፀም ይገደዳሉ።

**ለምሳሌ ያህል ወ/ሮ አዜብ ወልዱ የሚከተለውን ብለዋል።**

በጥቅምት፣ ሕዳር እና ታህሳስ አዝመራው ሁሉ ሰአት ስለሆነ ሁሉም የጥራጥሬም ሆነ ሌሎች ምርቶች እንደልብ የሚያገኙት እና አዝመራ ተሰብስቦ የሚገባበት በዚህ ወቅት በመሆኑ ሰው ሁሉ ብዙ ስራ ስለማይኖረው በሀገረሰባዊ አስተዳደር መሪ (ኦና) መረጣ ክዋኔ ላይ በንቃት ይሳተፋል። (ወ/ሮ አዜብ ወልዱ ፣08/06/08፣)

የሀገረሰባዊ አስተዳደር መሪ (ኦና) መረጣ ክዋኔ የሚፈፀምበት ወር እና ቀን ከተወሰነ ቡኀላ የየአከባቢው ተወካዮች የሚሰበሰቡበት ጠቅላላ ጉባኤ ይጠራና ሁሉም እንደተገኙ እጩዎቻቸውን ያስተዋወቃሉ። አንድ እጩ ሌላ ተወዳዳሪ ከሌለውና ተቃዋሚ ከሌለ ተወካዮቹ ብቸኛውን እጩ ላይ የሹመት ክዋኘ ይፈፃሙ ነበር። ከአንድ በላይ እጩዎች ሲኖሩ ግን ተወዳዳሪዎቹ በትልቅ ዛፍ ጥላ ሥር ጎን ለጎን ይቀመጣሉ። በመቀጠልም ተወካዮቹ ከትናንሽ እጸዋት የተቀነጠሱ ቅጠል (የምርጫ ካርድ እንደማለት ነው) ይታደሉና በዕጩዎቹ ፊት ተሰልፈው እያንዳንዳቸው የታደሉትን አንድ የምርጫ ቅጠል በመረጡት ዕጩ ፊት እያስቀመጡ ያልፋሉ። ሁሉም መራጮች ምርጫቸውን ሲጨርሱ ከእያንዳንዱ እጩ ፊት-ለፊት የሚገኙት ቅጠሎች ይቆጠራሉ። በዚህ የድምጽ አሰጣጥ ሥርዓት አብላጫውን ድምፅ ያገኘ ኦና ተብሎ ይታወጃል።

የቅጠሉ በተመራጩ ላይ ማኖር ሶስት ትርጉሙ እንደነበረው መረጃ አቀባይ አባ ጥዑም በርሀ በመቐለ 15/08/2016 ዓ/ም ይናገራሉ።

1ኛዉ ትርጉሙ ጎዱፍ ሁሉ ነገር እንሚቋቋም ሁሉ አንተም እንደ ጎዱፍ ሆነህ ሁሉንም ነገር በትእግስት ተቋቍመህ እንዲትመራን ምኞታችን ነው የሚል ነው።

2ኛዉ ትርጉሙ እንደዚህ ቅጠል ለም ሁን፣ እኛን የሚጠቅም ሰዉ ሁን የሚል ምርቃት የያዘ ድርጊት ነዉ።

3ኛዉ ትርጉሙ ደግሞ እንደ ምርጫ ካርድ በመጠቀም ዕጩዎቹ ያገኙት ትክክለኛ ድምፅ ብዛት መለያ ዘዴ መሆኑ ነዉ።

ከሶስቱም የቅጠል ትርጓሜ መረዳት እንደሚቻለው ማህበረሰቡ አንዱ ለአንዱ በሰጠው ስልጣን ይብዛም ይነስም በታማኝነትና ትዕግስት የማገልገል ግዴታ እንዳለበትና ይህ ሳይሆን ስቀር በተመረጠው አካል ላይ የነበረው ማህበራዊ እምነት እና ተስፋ ባለመተግበሩ በማህበረሰቡ የተሰጠው ቦታ በቀጥታ እንደሚያጣ ነው።




ምስል አንድ:-ህዝቡም አንድ በአንድ በገዛ ፍቃዱ ደስ እያለው መሪውን መምረጡን ለማሳየት ቅጠል በተመራጩ ላይ ስያኖር።






ምስል ሁለት:-ህዝቡ በገዛ ፍቃዱ ደስ እያለው መሪውን መምረጡን ለማሳየት ባህላዊ መንገድ ደስታዉ ስገልጽ ያሳያል። /

ከዚህ በላይ እንደማሳያ የቀረቡ ምስሎች በ2006ዓ/ም በኢሮብ ብሔረሰብ ትግራይ ቴሌብዥን ከሰራው ዘጋቢ ፊልም የተወሰዱ ናቸው/

ማህበረሰቡ ሀገረሰባዊ አስተዳደሪ መሪው /ኦና/በመረጠበት እለት የደስታው መገለጫ መንገዶች ከሆኑት ባህላዊ ጨዋታዎቹ መካከል **በሆራ እና ዓዳር** ይገልፃል።

ሆራ በቡድን የሚከወን መሪ እና ተቀባይ ያለው በባህላዊ የደስታቸውና ጀግንነታቸው ስሜት የሚገልፁበት ጨዋታ ነው።

| **መሪ** | **ተቀባይ** |
| --- | --- |
| 1.ናኑ ኡጉነክ ኡጉተ ጉማ | ናኑ ኡጉነ |
| እኛ ተነስተናል ተነስ ቁራ | እኛ ተነስተናል |
| ጉማ ናሞል ገደ | ኢላልናም ሊኖ |
| ተከተለን ቁራ | የተማመነው አለን |
| 2. ኣሀየ ጉማይቶ | ጉማ ሓይሳም ናዲገ |
| ሆየ ቁራ | ቁራን የሚያጠግብ እኛ እናውቃለን |
| 3.ኣዳል ኖክ ሞቢና | ሑዳዲነህ ናነ |
| በመሀላችን እንዳትወርዱ | ተዘጋጅተናል |
| ኣብለ ሊቶነ | ኣብለ ሞንናን ማራ |
| ታያላቹህ | ያላቹህ ካላችሁ |
| ዓላማለ ጉማይ ዓላማለ ሆየ | ኣሃይ ጉማይ ዓላማለ |
| ጉዳይ አለን ኑ ቁራ ተከተሉን | አዎ ጉዳይ አለን |
| ሳናዲረ ኖህ ማታነ | ሳናዲረ |
| ለምን አንድ ነን አትሉም | አንድ ነን |
| ነምገዐክ ዲላለ | ሳናዲረ |
| ለጦርነት እንደ ንብ ነን | አንድ ነን |
| ያዶ ዓሲምማለ | ሳናዲረ |
| የጀግኖች ልዶች ነን | አንድ ነን |
| ነመተም ኣካለ | ሳናዲረ |

| | |
|---|---|
| እኛ አንድ ነን | አንድ ነን |
| አና ለም | ሳናዲረ |
| መሪ ያለን | አንድ ነን |
| ዋካሪ ሑልካለ | ሳናዲረ |
| እንደ ተኩላ ተንኮለኞት ነን | አንድ ነን |
| ዋዓጊ ፊድቶለ | ሳናዲረ |
| እንደ ጦጣ እንዘላለን | አንድ ነን |
| ሉባክ ዒምቢሮለ | ሳናዲረ |
| እንደ አንበሳ ሃይል አለን | አንድ ነን |
| ኢጊድ ቃሚያለ | ሳናዲረ |
| እንደ እንቁራሪት ተናካሽ ነን | አንድ ነን |
| ላዓኒ ዊኮለ | ሳናዲረ |
| እንደ ንስር ንቁ ነን | አንድ ነን |
| ዳታሊ ሒንዘለ | ሳናዲረ |
| እንደ እባብ መርዛም ነን | አንድ ነን |
| ኣይድኩም ጎምቦለ | ሳናዲረ |
| አለን በሉ ወጣት | አንድ ነን |
| ማዳጋይ ማብሎለ | ሳናዲረ |
| መሪዎቻች ራእይ አላቸው | አንድ ነን |
| ኒናባም ረዳለ | ሳናዲረ |

| | |
|---|---|
| ወላጆቻችን ሰርአት አላቸው | አንድ ነን |
| ኒዒንዳም ቢልዓለ | ሳናዲረ |
| ልጆቻችን ኩራት አላቸው | አንድ ነን |
| ኒሳዮ ሖላለ | ሳናዲረ |
| ሴቶቻችን ብልህ ናቸው | አንድ ነን |

በማለት አንድነት እንዳላቸው እና በሰርአትና መሪያቸዉ እንደሚኮሩ እንዲሁም ማንም ሊያጠቃቸው ብፈልግ ተባብረው እንደሚመክቱት በዚህ ባህላዊ ጨዋታተው ያሳያሉ።ይህ ጨዋታ አባቶች እና ወጣቶች በህብረት ከተጫወቱ ቡኋላ ለሁሉም ህዝብ የተዘጋጀው ምግብ እና መጠጥ ይቀርባል። የተዘጋጀው ስጋ እና ጤጅ እየተበላ በመሀል በማህበረሰቡ በእድሜ ባለጸጋነትና በአንደበተ ርቱእነት ከሚታወቁ አባቶች መካከል አንድ በአንደ እየተነሱ ለተመረጠው መሪ እና ማህበረሰብ ያላቸው ክብር እና ቦታ የሚገልጹ ስነ ቃላት ይቃኛሉ።

ለምሳሌ ያህል ለኦና ፍስሕ እና ኦና ኢስማዕል የቀረበ ዓዳር/ሙገሳ/

| | |
|---|---|
| 1. ኦና ፉሱሕ ዒሊስ ዳኒያ | ኦና ፍሱሕ ትልቅ ዳኛ |
| ተከዘ ሚላሳል ዳኒያ | እስከ ተከዜ ምላሽ ይዳኛል |
| ሓነይቲ ኣራሕኮ ከናን ፊያ | ከበቀለኛ መንገድ እሾህ ያነሳል |
| ኦኒ ሰርዓት ነፍቱላ በያ። | በኦና ሰርአት ህዝቡን ይመራል። |
| 2.ኦና ፉሱሕ ባዳ ስብሓቶ | የኦና ፍሱሕ ልጅ ስብሀት |
| ኣቱ አድ ኣሰምኮ ዓጋብ ሳቶ | አንተ በዋልከበት ሰላም ሙሉ |
| ኣኑ ዋየም ዳጎሚህ ሓቶ። | እኔ ያጣሁት አንተን የመሰለ። |
| 4.ኦና ኢስማዒል ባዳ ዓብዳላ | ኦና ኢስማዕል የዓብደላ ልጅ |
| ኑጉሱል ያውዐ ሳረጋላህ | ንጉስ ይቀበለዋል በሰረገላ |
| ጉባል ጋሓዶ ሳማሃና | እሱ ባለበት ሰላም ይዘመራል |

ለምግብ በምስሉ እንደሚንመለከተው በእየአካባቢው ሁሉም የየራሳቸው ከብት ያርዳል።



ለተመረጠዉ መሪ እና በክብር ለታደሙ እንግዶች የሚቀርብ  ከስጋ የሚዘጋጅ ባህላዊ ምግብ/ጊዕዝም/



ሀገረሰባዊ መሪ/ኦና/ ተመርጦ የምግብ እና መጠጥ መስተንግዶ ከተከናወነ ቡኃላ ከተመረጠበት ቀን ጀምሮ ባለስልጣንና የመረጠው ማህበረሰብ መሪ እንደሆነ ከባለጸጋ አባቶች ወይም የቀድሞ ሀገረሰባዊ መሪ/ኦና/የነበረ ተነስቶ ለተመረጠውና ህዝቡ መልእክት ያስተላልፋሉ። የተመረጠው መሪ በኦና ሰርአት መሰረት በየአካባቢው እሱን ወክለው ህዝቡን በመምራት የሚያግዙት ስራ ፈፃሚዎች የመምረጥ ስልጣን እንዳለው በመግለፅ ስራ ፈፃሚዎች መርጦ ወደ ተግባራዊ የመሪነት ተግባር መግባት እንዳለባቸው ለመሪ አሳስበው እና መልካም ምኞት ተመኝቶው ሀገረሰባዊ የመሪ ሹመት ክዋኔ ያጠናቅቃሉ።

### 4.3.2 ምስረታ ካቢኔ

በዘመናዊው ሰርዓት የኢትዮጵያ ህገ መንግስት ልክ ጠቅላይ ሚንስተር በፓርላማ ከተመረጡ ቡኋላ የራሳቸውን ካቢኔ ወይም ሰራ ፈጻሚዎች እንደሚመርጡ ሁሉ ኦና ከተመረጠ ቡኋላም በማግስቱ ሁሉም የማህበረሰብ ጉዳዮችን ብቻዉን መፈጸም ስለማይችል ተጠሪነታቸው ለእሱ ሆኖ ከተለያዩ አከባቢ የህግ አማካሪዎችና ፈጻሚዎች ለመሆን አቅም ያለባቸዉ ይሾም እንደነበረ ከመረጃ ሰጪዎች መካከል አንዱ የሆኑት መምህር ዝግታ በርሀ ይናገራሉ።

ከዚህ ሀሳብ መረዳት እንደሚቻለዉ የኢሮብ ብሔረሰብ ባህላዊ አስተዳደር ሰርአት ወይም ኦና ሰርአት በባህሪዉ እና ይዘት አተገባበሩ የዴሞክራሲያዊ ህገ መንግስት ይዘትና አተገባር ሂደት

የተከተለ እንደነበረ ሲሆን ለዚህ ማሳያ ደግሞ ፍትሓዊ የስልጣን ክፍፍልና ተጠያቅነትን ያካተተ ሰርአት መሆኑ ነው።

4.3.3 የኦና ስልጣን ዘመን

ኦና ተጠሪነቱ ለመረጠው ህዝብ ሆኖ ነገር ግን ስልጣን ዘመኑ በህግ የተቀመጠ አልነበረም። የኦና ስልጣን ዘመን የሚወሰነው ባለዉ ህዝቡን የመምራት ጥበብ፣ቅንነትና ተኣማኒነት ሆኖ ከስልጣኑ የሚወርደውም የመረጠው ህዝብ በእሱ የመምራት ጥበብና አቅም ላይ እምነት ሳይኖረው ስቀር፣በህመምና በእድሜ መግፋት ስሆን ኦና ከስልጣን የወረደው በህመምና እድሜ መግፋት ከሆነ በሚደረጉ የእርቅ ጉዳዮች እና አስተዳደር ዙርያ ምክረ ሀሳቡ የመስጠት እድል በማህበረሰቡና በአዲሱ ኦና ይሰጠዉ ነበር ይላሉ መረጃ አቀባይ አቶ ሃ/ማሪያም ተስፋይ።

በኢሮብ ሕግ መሰረት አንድ ሰው በአከባቢዉ ከፍተኛ ባለስልጣን (ኦና) ፍትሕ እንደተነፈገው ሆኖ ከተሰማው በይግባኝ ወደ ምክር ቤቱ የመውሰድ ሙሉ መብት ነበረው። ምክር ቤቱ ጉዳዩን በጥልቀት ከመረመረ በኋላ ባልስልጣኑ ስሕተት ፈጽሟል ብሎ ካመነ ከፍተኛ መሪውን ከስልጣን የማውረድና አዲስ ኦና/መሪ እንዲመረጥ የማድረግ ስልጣን ነበረው። ኦናው ጥፋተኛ ሆኖ ካልተገኘ ግን በስልጣኑ ላይ እንዲቀጥል ይደረጋል። የኢሮብ ሕግ ማህበረሰቡ ውስጥ ለፖለቲካ አስተዳደርና ግጭትን ለመፍታት መሰረት ሆኖ አገልግሏል።

አፄ ኃይለስላሴ አጠቃላይ የሆነ የተማከለ መንግሥት እስከመሰረቱ ድረስ ኢሮብ ከማዕከላዊ መንግስት ቀጥታዊ ቁጥጥርና ከጎረቤት የአከባቢ ህዝቦች ጣልቃ ገብነት ራሱን ተከላክሎ ይኖር ነበር። የኢሮብ ህዝብ የፖለቲካ ታሪክ ሁለት እኩል አስፈላጊ የሆኑ ገጽታዎችንያካተተ ነው የነበረው። እነዚህም ራስን በራስ ማስተዳደር ልዕልና ማስጠበቅና ለኢትዮጵያ ሃገራዊ አንድነትና ለንጉሡ ሥልጣን ዕውቅና መስጠት ነበሩ።

ሊዮ ራይኒሽ የተባለ ኦስትሪያዊ ምሁር በ1878 በታተመው 'The Language of Irob-Saho in Abyssinia' በሚል አርስት በጀርመንኛ በጻፈው በ1878 በቬና በታተመው መጽሐፉ በ19ኛው ክፍለ ዘመን አካባቢውን በጎበኘበት ወቅት "ኢሮብ በህዝብ ተወካይ ምክር ቤት በተመረጡ መሪዎች የሚተዳደር ራስ ገዝ የሆነ የኢትዮጵያ አካል ነበር፣ እንዲሁም የተመረጡት ከፍተኛ አመራሮች በምክር ቤቱና በህዝቡ ፊት ተጠያቂዎች ነበሩ" ብሎ ጽፏል። መረጃ አቀባይ አባ ጥዑም በርሀ በመቸለ 15/08/2016 ዓ/ም ይናገራሉ።

ከላየኛዉ ገለጻ መረዳት እንደሚቻለዉ በኦና ሰርአት የኦና ወይም የመሪ ሰልጣን ዘመን በአመታት የሚወሰን ሳይሆን የመሪዉ የስልጣን ቆይታዉ በማህበረሰቡ በወጣዉ እና በተሰጠዉ ስልጣን መጠን በቅንነት እና በታማኝነት ማህበረሰቡ እስከ እስከአገለገለ ድረስ መሆኑን ነው።

# ምዕራፍ አምስት

## 5.1 ማጠቃለያ

ይህ ጥናት በኢሮብ ብሔረሰብ የሀገረሰባዊ አስተዳደር መሪ (ኦና) መረጣ ስርአተ-ክዋኔ ትንተናያደረገ ሆኖ የጥናቱ ዋና ዓላማ በኢሮብ ብሔረሰብ የሀገረሰባዊ አስተዳደር መሪ (ኦና) መረጣ ስርአተ-ክዋኔ ላይ አውድ ተኮር ትንታኔ ማድረግ ሲሆን አውድን መሰረት ባደረገ መልኩም ክዋኔው በቅደም ተከተል ተገልፀዋል። በኢሮብ ብሔረሰብ የሀገረሰባዊ አስተዳደር መሪ (ኦና) መረጣ ስርአተ-ክዋኔ ጉዳዩች የሚከናወኑበት ሂደት ላይ የሚታዩ ትዕምርቶች ብሔረሰቡን የመግለጽ ሚናቸው ከፍተኛ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል። በእያንዳንዱ ክዋኔ የሚከናወኑ ክንውኖች የተግባራዊ መዋቅር የተከተሉና በድግግሞሽ በማህበረሰቡ ዘንድ የተለመዱ ናቸው። በመሆኑም የት ቦታ ምን ማደረግ እንዳለባቸው ያውቃሉ። በኦና ሰርአት መሰረት የኦና ሹመት ሰርአተ ክዋኔ ከመድረሱ በፊት እንዲሁም የኦና ሹመት ሰርአተ ክዋኔ በሚከናወንበት ወቅት ማን ምን ማድረግ እንዳለበት፣የሚለበሱ አልባሳት፣የሚበሉ ምግቦች እየተከናወነ ያለውን ሂደት የሚጠቁሙ መሆናቸው ጥናቱ አመላክቷል።

## 5.2 የይሁንታ ሀሳብ

በመሆኑም በኢሮብ ብሔረሰብ ባህል ዙሪያ ጥናት የሚያደርጉ አጥኚዎች በኦና ሰርአተ ክዋኔ ወቅት የሚታዩትን ሌሎች የፎክሎር ዘውጎች በመመርመር በማህበረሰቡ ዘንድ ለምን እንደሚከወኑና ምን ፋይዳ እንዳላቸው ቢፈትሹ ማህበረሰቡንና ባህሉን በሚገባ መረዳትና መግለጽ ይችላሉ የሚል እምነት አለኝ።

የኦና ሀገረሰባዊ መሪ አመራረጥ ሂደት የኢሮብ ብሔረሰብ ማህበራዊ ፍልስፍናና ሁለንተናዊ ምንነት መገለጫ ሆኖ ለዘመናት የኖረ፣ አሁን በሀገርቷ ተግባር ላይ እየዋለ ላለዉ ዴሞክራሲያዊ ህገ መንግስት እና መሪ አመራረጥ መሰረት የሚሆኑ መርሆችና ህጎች ያሉት፣ በትግበራ ላይ ያለዉን ህገ የማይጻረር ባህላዊ ሰርአት እንደ መሆኑ መጠን የሚመለከታቸዉ የብሔረሰቡ የባህልና ማህበራዊ ፍትህ አካላት በከፍል ትግበራ ላይ የሚገኘዉን ባህላዊ የኦና ሰርአቱ ወደ ተሟላ ቁመና እንዲመለስ የበኩላቸዉን ሚና ቢወጡ ባይ ነኝ።

**ዋቢ ጽሑፎች**


ለቺሳ አሰፈ። "በጨሊያ አውራጃ ስለውቃቢ ያለው እምነትና የእምነት መገለጫ ግጥሞች"። የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነ-ፅሁፍ ትምህርት ክፍል፣ለመጀመሪያ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናታዊ ፅሁፍ፣አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣1982 ዓ.ም.

ሰለሞን ተሾመ። (2007)። ፎክሎር ምንነቱና የጥናቱ የትኩረት አቅጣጫ። አዲስ አበባ፤ፋሪኢ.ስት ትሬዲንግ ኃላ.የተ.የግ.ማ።

በርሀ ዝግታ።መቦቆልን ባህልን ህዝቢ ኢሮብ። ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት፣ አ/አበባ፣2000 ዓ.ም።

ተመስገን ፊንታዬ። "የዛር ትውፉትና በውስጡ የሚገኙ ትያትራዊ አላባዊያን በራያና ቆቦ አካባቢ"። ትያትርና ጥበባት ትምህርት ክፍል ለአርትስ ባችለር ዲግሪ ማሟያ የቀረበ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ 1995 ዓ.ም.።

እንዳልካቸው አካሉ። "በምዕራብ ሀረርጌ (ጨርጨር) አካባቢ የአወሊያ ቤት የልመና ግጥሞች ይዘት ትንተና"። የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነ-ፅሁፍ ትምህርት ክፍል፣ ለመጀመሪያ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናታዊ ፅሁፍ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ 1993 ዓ.ም።

ወልዱ ይንገሱ። "የዛር ትያትራዊ ክንውን ሲምዩቲክ ጥናት"። የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነ-ፅሁፍ ትምህርት ክፍል፣ ለመጀመሪያ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናታዊ ፅሁፍ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣1991 ዓ.ም.

ዘቢባ መንግስቴ "በወረባቦ ወረዳ የገፈራ ስርአተ-ክዋኔ" ለድህረ ምርቃ፣ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነ ፅሁፍ ትምህርት ክፍል፣አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ 2008 ዓ.ም.።

ዝግታ ሓድጉ።ዋንታዊ ምሕደራ ኢሮብ። ደስታ ማተሚያ ቤት፣ መቐለ፣2008 ዓ.ም።

የውልሰው ላለለት። "አዋቂና የጥንቆላ ስራው በደብረ ማርቆስ አካባቢ"። የዲግሪ መመረቂያ ፅሁፍ፣ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነ ፅሁፍ ትምህርት ክፍል፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ 1992 ዓ.ም።

Bell, Catherine. (1997). Ritual Perspectives and Dimensions. New York, Oxford University Press.

Ben-Amos Dan. (Apr. - Oct., 1993)."Context" in Context. Theorizing Folklore: Toward New Perspectives on the Politics of Culture. Western Folklore, Vol. 52, No. 2/4, pp. 209-226.

Boyer, Pascal and Lie´nard, Pierre. (2006). Why ritualized behavior? Precaution Systems and action parsing in developmental, pathological and cultural rituals. United state of America,

Dorsen, M. Richard. (1972. Folklore and Folklife: An Introduction to. Chicago: The University of Chicago Press.

Fischer, J.L."The Sociopsychological Analysis of Folktales." The Journal of Current Anthropology, Vol. 4, No. 3 (Jun., 1963), p. 235-295, The University of Chicago Press, http:// WWW.Joster.org/ stable/URL.

Goldstein, Kenneth. A Guide for field works in folklore. The American folklore society: folklore association Inc. 1964.

Kumar Ranjit. Reseach Methodology: A setp-by- step guide for beginners

(3rdedn). London: SAGE Publication Ltd, 2011.

Martha, C. Sims and Martine, Stephens. (2005). Living Folklore; an Introduction to the Study of People and their Traditions. Utah: Utah State University Press.

Malinowski, bronislaw.1044.A scientific Theory of culture. Chapel Hill; university of Northern Carolina press.

Mazama.Ama and Molefikete Asante. (ed).(2009). Encyclopidia of African

Relgion. Sage Publications, Inc.

Sims, Martha C. and Martine Stephens. Living Folklore: An Introduction to the study of People and their Traditions. Logan, Utah: State University

Press, 2005.

https ://advocacy.irob people. Org/

Irob mountain livelihood zone February 200-4

https://www.youtube.com/watch?v=vh0JbBuRmRw

አባሪ1

የመረጃ አቀባዮች ስም ዝርዝር

| ተቁ | ስም ዝርዝር | ጾታ | እድሜ | አድራሻ | ቀበሌ | ማብራሪያ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 1. | መ/ር በርሀ ዝግታ | ወ | 70 | ወረዳኢሮብ | ዓሊተና | |
| 2. | ወ/ሮ ለምለም ደበሱ | ሴ | 52 | ወረዳኢሮብ | ኣራዕ | |
| 3. | ወ/ሮ ደስታ ተስፋይ | ወ | 47 | ወረዳኢሮብ | ዓ/ኩማ | |
| 4. | ብጹእ አቡነ ተስፋስላሴ ተስፋይ | ወ | 69 | ወረዳኢሮብ | ዓሊተና | |
| 5. | መ/ር ሃይለ ተስፋይ | ወ | 55 | ወረዳኢሮብ | ወርዓትለ | |
| 6. | አቶ ሃ/ማሪያም በርሀ | ወ | 61 | ወረዳኢሮብ | ወርዓትለ | |
| 7. | መ/ር ሰለሙን ሃይሉ | ወ | 65 | ወረዳኢሮብ | ዓሊተና | |
| 8. | አቶ አለማ ገብራይ | ወ | 52 | ወረዳኢሮብ | ወርዓትለ | |
| 9. | ወ/ሮ አዜብ ወልዱ | ሴ | 48 | ወረዳኢሮብ | ሓራዘሰብዓታ | |
| 10. | ወ/ሮ መድህን ተስፉ | ሴ | 45 | ወረዳኢሮብ | እንዳሞሳ | |
| 11. | አቶ ህሉፍ አብርሃ | ወ | 65 | ወረዳኢሮብ | እንዳልገዳ | |
| 12. | አቶ ተስፋይ ዮሃንስ | ወ | 62 | ወረዳኢሮብ | ሓራዘሰብዓታ | |
| 13. | አባ ጥዑም በርሀ | ወ | 79 | ወረዳኢሮብ | ዓሊተና | |
| 14. | አባ ብስራት ተሰማ | ወ | 58 | ወረዳኢሮብ | ዓ/ኩማ | |
| 15. | ቀሲስ አረጋዊ ንጉሰ | ወ | 75 | ወረዳኢሮብ | ሓራዘሰብዓታ | |
| 16. | መ/ር ሓጎስ ጸጋይ | ወ | 57 | ወረዳኢሮብ | እንዳገዳ | |

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 17. | አቶ ኢ.ያሱ ምስግና | ወ | 55 | ወረዳኢ.ሮብ | እንዳገዳ | |
| 18. | አቶ ዝግታ ሓድጉ | ወ | 68 | ወረዳኢ.ሮብ | ደዉ.ሃን | |
| 19. | አቶ ካሓሰ ፍትዊ | ወ | 46 | ወረዳኢ.ሮብ | ደዉ.ሃን | |
| 20. | አቶ ፍሱሕ ስብሓት | ወ | 58 | ወረዳኢ.ሮብ | እንዳሞሳ | |
| 21. | አቶ ንጉሰ ተስፋይ | ወ | 80 | ወረዳኢ.ሮብ | እንዳገዳ | |
| 22. | ወ/ሮ ትሐሽ በርሀ | ሴ | 71 | ወረዳኢ.ሮብ | ዓ/ኩማ | |
| 23. | ወ/ሮ ማና ተስፋይ | ሴ | 65 | ወረዳኢ.ሮብ | ዓ/ኩማ | |
| 24. | ወ/ሮ አብርሄት ሓጎስ | ሴ | 45 | ወረዳኢ.ሮብ | እንዳሞሳ | |
| 25. | አቶ አሰፋ ካሕሳይ | ወ | 66 | ወረዳኢ.ሮብ | ኣራዕ | |
| 26. | ወ/ሮ ማና ንጉሰ | ሴ | 48 | ወረዳኢ.ሮብ | ደዉ.ሃን | |
| 27. | ወ/ሮ አበባ ፍሱሕ | ሴ | 46 | ወረዳኢ.ሮብ | ወርዓትለ | |
| 28. | ወ/ሮ ንግስቲ ወ/ሚካኤል | ሴ | 46 | ወረዳኢ.ሮብ | ሓራዘሰብዓታ | |
| 29. | መ/ር ተስፋይ ረዳ | ወ | 78 | ወረዳኢ.ሮብ | ደዉ.ሃን | |
| 30. | መ/ር ጥዑም መድህን | ወ | 57 | ወረዳኢ.ሮብ | እንዳሞሳ | |
| 31. | ወ/ሮብስራትገብራይ | ሴ | 48 | ወረዳኢ.ሮብ | ዓ/ኩማ | |
| 32. | ወ/ሮደስታ ሓጎስ | ሴ | 45 | ወረዳኢ.ሮብ | እንዳገዳ | |
| 33. | ወ/ሮንግስቲፍሱሕ | ሴ | 45 | ወረዳኢ.ሮብ | ዓሊ.ተና | |
| 34. | ወ/ሮወይኒ ባራኪ | ሴ | 47 | ወረዳኢ.ሮብ | እንዳሞሳ | |
| 35. | ወ/ሮለተብርሃን ሃይሉ | ሴ | 45 | ወረዳኢ.ሮብ | እንዳሞሳ | |

## አባሪ 2 አጥኚዉ ከመረጃ አቀባዩች ጋር



አጥኚዉ መረጃ በሚሰበስብበት ስፍራ።እንዲሁም ከኢሮብ ልማት ማህበር በመተባበር የኦና ሰርዓትን በዶክሜንቴሪ ፊልም መልክ ለመሰነድ ቀረጻ ላይ።











የመሪ/ኦና/ ካባ          ባህላዊ ጨዋታ ስጫወቱ አባቶች እና ወጣቶች የሚለብሱት ባህዊ ካባ





በ2017 ዓ/ም መስከረም ወር ላይ በኢሮብ ልማት ማህበር አስተባባሪነት የኦና ሰርዓት ህገ ደንቢ ላይ ዉሱን የደንብ ማሻሻያ ለማድረግ ከማህበረሰብ ተወካዮች ጋር ዉይይት ሲደረግ።